



ደሴ ከተማ የሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ከህንፃ በልማት ተግባር ላይ

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ



በኢየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም ።

ቁጥር ፹፫

ነሐሴ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም በሰጠ አበበ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

## ማ ው ጫ

**አርእስት ፤** — **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........................................ ፩
ጽድቅና ሰላም ተስማሙ ........................................ ፬
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................................ ፭
የቂሣርያ ጥያቄ ........................................ ፯
ደብረ ታቦር ........................................ ፰
ዜና ዕረፍተ ለተክለ ሃይማኖት ........................................ ፲
ዜና ሊቃውንት ........................................ ፲፫
ቅድስት እንባመሪና ........................................ ፲፭
ልደተ ሙሴ ........................................ ፲፮
የግብርና በረከት ........................................ ፲፯
የሌዊ በትር ........................................ ፲፰
ለዶርዜ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን
ኤሌክትሪክና የድምፅ ማጉሊያ መግባቱ ተገለጠ ........................................ ፳
ዜና ዕረፍት ........................................ ፳፩
ዳግም ምጽአት ........................................ ፳፬
የዘመን አቆጣጠር መቼ ተጀመረ ? ........................................ ፳፭


ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ የእግዚአብሔር በረከት ይድረሳችሁ በጥር በየካቲት ፤ በመጋቢት ፲፱፻፸፮ ዓ.ም እትማችሁ "ማነን ላግባ" በሚል ርዕስ በቀለመ ወርቅ መአሾ የተጻፉትን ተከታታይ ጽሑፎች በጥሞና አንብበናል በዚህ ጽሑፍ ጥልቀትና ምጥቀት በሻገር ለስነ ጽሑፋዊ ውበት አድናቂዎች ነን።

በማህበራዊ ኑሮ አንዋር ላላገቡ ወይም ስለ ሌሎቹም ለተሳሳቱ በጥቅሉም የመሰሎችን በር ስለሚያንኳኳ ውስጣዊ ይዘቱ በተለያዩ ሥነ ልቡናዊ መንገዶች ተሠንጥቆ የወጣ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለአዲስ መንፈሳዊና ከዚያም ባሻገር በሥጋዊ ሕይወት ላሉ አዲስ የባህል መሠረት በመሣል የማህበራዊ ኑሮ ችግሮችን በጥበባዊ አዝማሚያ ለመወጣት የአላትን ጥሩ አስተሳሰብ እንደሚአበስር ተገንዝበናል ።

በቀለመ ወርቅ መአሾና በሌሎቹ ደራስያን ማህበራዊ ነክ ተመሣሣይ ጽሑፍ እንደሚኖራችሁ እየተመኘን ስለቀለመወርቅ መአሾ ብትገልጹልን ? የቤተ ክህነት አገልጋይ ወይስ ምዕመን ? በመጨረሻም ካህናቱ በሚጽፏቸው መንፈሣውያን ጽሑፎች ስነ ጥበባዊ ውበት እናደንቃለን ።

ከከፍተኛ ፳፩

የመጽሔታችሁ የቡድን አንባቢዎች

የከፍተኛ ፳፩ የመጽሔታችን አንባቢዎች ስለአቀረባችሁልን ሰላምታ እኛም አጸፋውን ይድረሣችሁ እያልን መጽሔታችንንም እየተከታተላችሁ ስለምታነቡልን እናመሰግናችኋለን ለወደፊቱም እያነበባችሁ ጥያቄዎችን ብትጽፉልን በደስታ እንቀበላለን ከዚሕ ላይ ግን ሣናሳስባችሁ የማናልፈው ነገር ቢኖር ከአሁን ቀደም ጥያቄ ስትጽፉ ሙሉ አድራሻችሁንና ስም ከነአባቱ እንድትጽፉ ይህ ባይሆን ግን ለጥያቄአችሁ መልስ እንደማንሰጥ ገልጸን ነበር እናንተ የመጀመሪያ ጥያቄ አቅራቢዎች ስለሆናችሁ የዛሬውን ተቀብለነዋል ለወደፊቱ ግን ሙሉ ስም ከነአድራሻ ከሌለው ጥያቄውን የማንቀበል መሆናችንን አሁንም ደግመን ልናስገነዝብ እንወዳለን ።

ከዚሕ ቀጥለን ወደጥያቄው እንመለስና የመጀመሪያው ጥያቄአችሁ የሚለው ስለ ቀለመወርቅ መአሾ ብትገልፁልን ነው የቤተክህነት አገልጋይ ወይስ ምእመን የሚል ሲሆን ቀለመ ወርቅ መአሾ ዜማና ቅኔ አዋቂ እንደመሆኑ መጠን ካህን እንጅ ምዕመን አይደለም ነገርግን በአሁኑ ጊዜ የዩኒቨርስቲ ተማሪ እንጅ የቤተ ክህነት ሠራተኛ(አገልጋይ) አይደለም ።

ቀለመወርቅ መአሾ አይነስውር ሲሆን ብሬል ተምሮ ይጽፋል ያነባል ይልቁንም ማንበብ ስለሚወድ ብዙ መጻሕፍትን ይከታተላል ይህንንም ከራሱ ጠይቀን ለመረዳት ችለናል ማነን ላግባ በሚለው ጽሑፍም መገመት ይቻላል እናንተም እንዳጠያየቃችሁ ጽሑፉን በጥሩ ሁኔታ የገመገማችሁት ይመስለናል ።

## ዜና ዕረፍት

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ወላጅ ዘመዶቿን እንዲሁም ድንገት ሳያስቡት ከመካከላቸው በመለየቷ የመረረ ልባዊ ጥልቅ ኀዘን የተሰማቸው የወልድ ዋህድ መንፈሳዊ የሰንበት ት/ቤት ወንድሞቿንና እህቶቿን እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያልን የዚህ ጽሑፍ አንባብያን ሁሉ የእህታችንን ነፍስ እግዚአብሔር ከቅዱሳን ጋር እንዲምርልንና በሷ እረፍት የመረረ ኃዘን የተሰማቸውን ሁሉ መጽናናትን እንዲሰጣቸው የሀሊና ጸሎት እንዲያቀርቡልን እየጠየቅን ፤ ጽሑፋችንን በዚሁ እናጠቃልላለን ደሴ መድኃኔዓለም

የወልድ ዋህድ የሰንበት ት/ቤት ጽ/ቤት

# ልማት በቤተ...

ከገጽ ፭ የዞረ

ጣቢያዎች ጥረት አድርገዋል ።

ከዚህ በላይ በርእሱ እንደተጠቀሰው፤ ስለአምስቱ የካህናት ማሰልጠኛዎች ዓላማና ተግባር በመጠኑም ቢሆን ጥቆማ እየተካሄደ ሲሆን ፤ እ.አ.ዘ.አ. በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ስለተፈጸሙት ዓበይት ተግባራት ከእያንዳንዱ የማሰልጠኛ ኃላፊ ዝርዝር መግለጫ በተጨባጭ እንደሚቀርብ ተስፋ እናደርጋለን ።

፬/ ስለሚኒ ፕሮጀክት ፤

በየአህጉረ ስብከቱና በአዲስ አበባም አካባቢ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የሚገኙት ካህናት ከመንፈሳዊው አገልግሎታቸው ጋር የልማት ሥራን በማካሄድ በአንፃሩ እንዲጠቀሙ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ልዩ ትኩረት በመስጠት ፤ ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር በጐአድራጊዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ የሚኒ ፕሮጀክትን ዓላማ በማስፋፋት ረገድ በተግባር እንዲተረጐም እ.አ.ዘ.አ. በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ወሰን የሌለው ጥረት አድርጓል።

በሚኒፕሮጀክት ዓላማ አንፃር አቅም በፈቀደው መጠን በየአህጉረ ስብከቱ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በጥናትና በእቅድ የተደገፈ ንድፈ ሃሣብ ሲቀርብ ፤ ቅደም ተከተሉ በመከተል የእርዳታ ገንዘብ ወጭ በማ ረግ፤

ሀ. የእህል ወፍጮ ገዝቶ ማ ቋም ፤

ለ. አነስተኛ የጎጆ እንዱስት ማቋቋም ፤

ሐ. በግብርና ረገድ በሬዎችንና የእርሻ መሣሪያዎችን ገዝቶ መስጠት ፤

መ. አልፎ አልፎም አብያተ ክርስቲያናትን ማሳነጽና ማሳደስ ፤

ሠ. ለንብ እርባታ ተገቢውን መሣሪያ መግዛት

ረ. መጠነኛ የከብት እርባታን ማደራጀትና የመሳሰሉትም ይገኙበታል ።

ይቀጥላል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# “ጽድቅና ሰላም ተስማሙ”

ጽድቅና ሰላም አብረው ሊፈጸሙ የሚገባቸው አስፈላጊዎች የሆኑ ምግባራት ናቸው ።
ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት ሥነ ምግባራት ዋነኛውን ክፍል ይዘውት የሚገኙትም ጽድቅና ሰላም ሆነው
እናገኛቸዋለን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ላይ ሕዝቡን ሰብስቦ ካስተማራቸው ዘጠኝ
የብፅዕና ትምህርቶች መካከልም “ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና ፣ ሰላምን የሚያ
ደርጉ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና” የሚሉ ቃላትን እናገኛለን ይህም ጽድቅና ሰላም ለሰው
አስፈላጊዎች መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው የማቴ.ወን ፣ ፭ ፣ ፮ - ፲ ።
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማውጣት ሲል ከሰማየ
ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫ት ወራት መኖሩ የታወቀ ነው ከም
ድር ላይ በግዘፈ ሥጋ ሲኖር ከሰዎች ጋር አብሮ በመብላትና በመጠጣት በመውጣትና በመውረድ ተርቧል ተጠ
ምቷል ከኃጢአት በስተቀር በሰው ልጆች ላይ የሚደርሰውን መከራ ሁሉ ተቀብሏል ።
ይሁን እንጂ ከአፉ የሐሰት ቃል ወጥቶ አያውቅም ይህንንም ሐዋርያው ጴጥሮስ በመልእክቱ ሲገልጽ
“የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌን ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከ
ራን ተቀብሏልና ፣ እርሱም ኃጢአትን አላደረገም ሐሠትም በአፉ አልተገኘበትም ፣ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳ
ደበም ፡ መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ራሱን አሳልፎ ሰጠ ለኃጢአት ሙተን ለጽድቅ እንድን
ኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ ብሏል ፩ኛ ጴጥሮስ ፪ ፣ ፳፩ - ፳፬ ።
ክርስቶስ በአይሁድ ምቀኝነትና ጥላቻ በተጠነሰሰ ሴራ ተይዞ በሐሠተኞች ምስክሮች ከተመሰከረበት
በኋላ የመጨረሻውን ፍርድ ለመቀበል አንድ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ፣ አንድ ጊዜ ወደ ጲላጦስ እየተመላለሰ ልዩ ልዩ
መከራ ቢደርስበትም አይሁድ መከራውን እንዲያቀሉልኝ በማለት የውሸት ቃልን ለመናገር አልሞከረም ።
በዚያን ጊዜ ፈራጅ ዳኛ በነበረው ጲላጦስ ፊት ቆሞ አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን ብሎ በጠየቀው ጊዜ
“እኔ በጽድቅ ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ፣ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከጽድቅ የሆነ ሁሉ ቃሌን ይሰ
ማል” በማለት ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ምክንያት በእውነት ገልጾ ተናገረ እንጂ የአይሁድን ጽዕለት ፈርቶ
እውነትን በሐሠት አልለወጠም ፣ ጲላጦስም ጽድቅ ምንድር ነው ብሎ በኢየሱስ አነጋገር ከመደነቅ በስተቀር
ሐሠት ሳይናገር በመቅረቱ አልተበሳጨም የዮሐንስ ወን. ፲፰ ፡ ፴፯ ።
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ የሞተው በአዳም አለመታዘዝ በሐሠት ወደ ዓለም
የገባውን ኃጢአት በጽድቅና በሰላም መልሶ በማስወጣት ሰውን የጽድቅና የሰላም ማደሪያ ለማድረግ ነው ይህን
ንም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች ጽፎ በላከው መልእክቱ “እንግዲህ በአንድ ሰው በደል ምክንያት ፍርድ ለኩ
ነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደመጣ በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ
ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ” በማለት ተናግሯል ሮሜ ፭. ፲፰ - ፲፱ ።
በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው መራራቅ በጌታችን በመድረኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት
እንደሚወገድና ጽድቅና ሰላምም በምድር ላይ እንደሚሰፍኑ የተገለጸለት ክቡር ዳዊት ቀደም አድርጐ “ምህረ
ትና እውነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላም ተስማሙ እውነት ከምድር በቀለች ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች እግዚአ
ብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል ምድርም ፍሬዋን ትሰጣለች ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል ፍለጋውንም በመንገድ ውስጥ
ያኖራል” በማለት ተናግሮ ነበር መዝ. ፹፬ ፡ ፲ - ፲፫ ።
ይህ የተነገረው ትንቢት አልቀረም ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሁሉም ፍጥረት ተደስተዋል ጽድቅና ሰላም
ም በምድር ሆኖአል ፣ ሐዋርያው “ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ አሁን ግን እናንተ በፊት
ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን
ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህ
ም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንምበመስቀሉ ገድሎ
በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ
ለእናንተ ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ” በማለት ጽድቅና ሰላም በክርስቶስ ደም መመሥረታቸውን ተናግሯል
ኤፌሶን ፪ ፡ ፲፪ - ፲፯ ።
ዓመት ፍዳና ዓመተ ኩነኔ አልፈው ዓመተ ምህረት ከተተካ ወዲህ በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰው ልጆችን ሁሉ በጽድቅና በሰላም ወደዘለዓለማዊ ድኅነት ትጋብዛለች ።
በሀገራችን ኢትዮጵያ የክርስትና እምነት የተሰበከው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ፴፭ ዓመት ሲሆን ትምህ
ርቱንም ያመጣው የኢትዮጵያ ንግሥት ጀንደረባ መሆኑን ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንረዳለን ።
ከዚያ ዘመን ጀምሮ የክርስትና እምነት ቀስ በቀስ መስፋፋት ይዟል በ፫ መቶ ዓመት በአባ ሰላማ ከሣቴ
ብርሃን አማካይነት ምሥጢረ ቁርባን እየተዘጋጀ ለምእመናን መሰጠት ጀምሯል ቀደም ብለው ታንፀው መሥ
ዋዕተ ኦሪት ሲፈጸምባቸው በነበሩት በአኩስም ጽዮን ፡ በጣና ቂርቆስ ፡ በተድባበ ማርያም ፡ በመርጡለ ማርያም
ወዘተ ቤተ መቅደሶች የኦሪቱ መሥዋዕት ቀርቶ የክርስቶስ ሥጋና ደም መሰጠት ይዟል ።
አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀደም ሲል ታንፀው በነበሩት አብያተ መቅደስ እየተገኙ በመቀደስ ሥጋው
ንና ደሙን ያቀብሉ እንደነበር ይነገራል ራሳቸው ይቀድሱበት የነበረውም ቅዳሴ በግሪክኛ ቋንቋ የተጻፈ ይባርኩ
በት የነበረው መስቀል እስከ ዛሬ ድረስ በተድባበ ማርያም ይገኛል ።
በአባ ሰላማ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት እየታነፁ አማንያን እየበዙ በመሄዳቸው ቀሳውስትና ዲያቆናትም
ሥልጣነ ክህነት እየተቀበሉ ቤተ ክርስቲያንን በንቃትና በትጋት ማገልገላቸውን ቀጥለዋል ይሁን እንጂ ከአባ
ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ዘመን ጀምሮ ሥልጣነ ክህነት የሚሰጡ ጳጳሳት ተሹመው የሚመጡት ከግብፅ በመሆኑ አን
ዳንድ ጊዜ የቀሳውስትና የዲያቆናት እጥረት እየደረሰ አብያተ ክርስቲያናት ከመዘጋት ይደርሱ እንደነበር ከታ
ሪክ እንረዳለን ።
የሚደርሰውን የካህናት እጥረት ለማስወገድ እንዲቻል ሊቃውንቱ ከመካከላቸው መርጠው ጳጳሳትን
ለመሾም አሳብ ቢያቀርቡም እርስ በእርሳቸው ባለመስማማታቸው ግብጻውያን ጳጳሳት ከአራተኛው መቶ ዘመን
ጀምሮ እስከ ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ
አመራር ሲመሯት ቆይተዋል ።
ነገር ግን ሊቃውንቱ በየጊዜው እየተሰበሰቡ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትን መርጠው ለመሾም ከመመ
ካከር አልቦዘኑም ቢሆንም በመካከላቸው ጽድቅና ሰላም ባለመኖራቸው ዓላማቸው ሁሉ ግቡን ሊመታ አልቻ
ለም ነበር ።
“ሣህሉ ለእግዚአብሔር በጊዜሁ” የእግዚአብሔር ይቅርታ በጊዜው ይፈጸማል ብሎ ክቡር ዳዊት እንደ
ተናገረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፵ ዓ.ም. ከሊቃውንቶቿ መርጣ ወደ ግብፅ በመ
ላክ ጵጵስና እንዲሾሙ ስታደርግ በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. የሊቀ ጵጵስናን ሥልጣን ተቀዳጅታለች ።
ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ፓትርያርኮችን ፣ ሊቃነ ጳጳሳትን ጳጳሳትን ፣ ኤጲስ ቆጶሳትን ከሊ
ቃውንቶቿ እየመረጠች ሹማለች አሁንም በመሾም ላይ ትገኛለች ወደፊትም ስትሾም ትኖራለች ።
በይበልጥ በዘመናችን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የምትመራው
ቤተ ክርስቲያናችን የጐደለውን እያሟላች የተሰነካከለውን እያስተካከለች የተዛባውን እያቃናች ወደፊት በመ
ራመድ ላይ ትገኛለች አገልጋዮቿ ካህናትም በንቃትና በትጋት በመሥራት ላይ ስለሚገኙ ወቅቱ ሁላችንም እንደ
ክቡር ዳዊት ጽድቅና ሰላም ተስማሙ እያልን ልንዘምርበት የሚገባ ዘመን ነው ።
የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓለ ሢመት መከበር ከጀመረ ፯ ዓመታት አልፈው ፰ኛው መጀ
መሩ ነው በምዋዕለ ሢመታቸው የተሠሩትን የሥራ ውጤቶች ስንመለከታቸው ከመዋዕለ ሢመታቸው አንሥቶ
እስከ አሁን ያለውን ዘመን ቢጨምሩ እንኳን ሊፈጸሙ የማይችሉ ሥራዎች ተከናውነው እናያቸዋለን ።
ነቢዩ ኢሳይያስ በተጠማ ላይ ውሀን ፣ በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈሳለሁና በፈሳሾችም እንደሚ
በቅሉ እንደ ዛፎች በሣር መካከል ይበቅላሉ ብሎ እንደተናገረው የወንጌል ትምህርት ያልደረሳቸው እንዲደርሳ
ቸው የብሉይና የሐዲስ ጉባኤ መምህራን በየቦታው እንዲያስተምሩ መንፈሳዊ መመሪያ ከመስጠታቸውም ሌላ
ሰባክያነ ወንጌል በየአህጉረ ስብከቱ እየተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ ሲያዝዙ ራሳቸውም ቢሆኑ በየአህጉረ ስብ
ከቱ እየተዘዋወሩ ከማስተማር የተቸገሩትን ከመርዳት ፡ ያዘኑትን ከማጽናናት የተቆጠቡበት ጊዜ አይገኝም ።
ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ በስብከተ ወንጌል ፣ በመጽሔቶችና በጋዜጦች በአስተዳደር በሰበካ
ጉባኤ ፡ በልማት ወዘተ የምታደርገው እንቅስቃሴ እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ጽድቅና ሰላምም በቤተ ክርስቲያና
ችን ተስማምተው በመምራት ላይ ናቸው ።
ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወደፊት ከአሁኑ የበለጠ መንፈሳዊ ሥራ ተደቅኖ እንደሚጠብቃት የታ
መነ ነው ፣ ቤተ ክርስቲያናችን የጀመረችውን ለመፈጸም ያቀደችውን ጀምሮ ለመሥራት የምትችለው በእግዚአ
ብሔር ፈቃድና በቅዱስነታቸው ጸሎት ጽድቅና ሰላም ሲስማሙ ስለሆነ ለቅዱስነታቸው ሰፊ ዘመናትንና ረዥም
ወራትን ለሀገራችን ጽድቅንና ሰላምን ይስጥልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንማፀናለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ከብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተ/ ጸሐፊ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትን ከመሠረቱት አንዷና የመጀመሪያዋ እንደመሆኗ ፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ አማካይነት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት እርዳታና በተከታዮች ልጆቿ ምዕመናን ድጋፍ የልማትን ፣ የተራድኦንና የመሳሰለውን ሥራ በማከናወን ላይ ትገኛለች ።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያም ይህን የልማትንና የዕድገትን ተግባር የሚያከናውነው የመምሪያው የሥራ አመራር ኮሚቴ በሚሰጠው መመሪያና በየዓመቱ በሚደረገው በኮር ኮንሰርሽየም ጉባዔ አማካይነት ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በሚመረጡ አባላት ሥራው እየተገመገመ ሕግ ባወቀው ኦዲተር በየዓመቱ ፍጻሜ የዓመቱን ሂሣብ እያስመረመረ በመሆኑ እስከ አሁን ድረስ ለኅብረተሰቡ በፈጸማቸው የተቀደሱ አገልግሎቶች መንፈሳዊ ርካታ የሚሰማው መሆኑን እየገለጽን ወደፊትም ሥራው እየጠነከረና እየሰፋ በሄደ መጠን ርዳታውም እየዳበረ እንደሚሄድ ተስፋ እናደርጋለን ።

መምሪያችንም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤትና ከሌሎች በጐ አድራጊዎች ጋር ያለው ኅብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደማንሰራራቱ ደረጃ የደረሰ ለመሆኑ በተጨባጭ የተረጋገጠ ሲሆን ፣ ይዘቱም ለወደፊቱ የበለጠ አበረታች እንደሚሆን እሙን ነው ።

በዚሁም መሠረት ፣ በአህጉረ ስብከት ደረጃና በአዲስ አበባ ከተማ ፣

ሀ/ ለአምስቱ የካህናት ማሰልጠኛ ዎች

ለ/ ለሚኒ ፕሮጀክት

ሐ/ ለተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግር ማስወገጃ

መ/ ለሰበካ ጉባኤ ማቋቋሚያ ማደራጃ

ሠ/ ለሰንበት ት/ቤት ማስፋፊያ

ረ/ ለመሠረተ ትምህርት ሥራ መደጐሚያ

ሰ/ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች

አቅም በፈቀደ መጠን የበጀትና የእርዳታ ገንዘብ ፣ የእህል ፣ የቁሳቁስና የመሳሰሉትን እርዳታ በመስጠት ከመቼውም ይልቅ እ.ኤ.ዘ.አ. በ፲፱፻፹፫ የበጀት ዓመት ከፍ ያለ እርዳታ በማበርከት ግቡን በመምታት ረገድ እጅግ ከፍ ያለ ተሳትፎ አካሄዷል ።

ይኸውም በየርዕሱ ወደፊት በይቀጥላል ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የሚተነተን ሲሆን ፣ በልዩ ልዩ የእርዳታ አሰጣጥ ረገድ በበለጠ መረዳት እንዲቻል አባሪዎቹን ቁጥር አንድንና ሁለትን መመልከት ነው ።

፩ኛ/ ስለ ካህናት ሥልጠና ፡

የብሔራዊቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕልውናን ለመጠበቅ አገልጋዮቿ ካህናት በየትምህርት ቤቱና በየማሰልጠኛው በመግባት አሳማዋን በመከተል ተልዕኮአቸውን አውቀው ስለ ሃይማኖታቸው ጥልቅ ዕውቀት በመቅሰም በልዩ ልዩ ሙያ ተሰማርተው ቤተ ክርስቲያናችንን ማገልገል እንዲችሉ ፣

ቀጥለው የተመለከቱት ማሰልጠኛዎች በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ቀደም ሲል ተቋቁመው እየሠሩ ነው ።

ሀ/ በዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ ፡ የሸዋ ፣ የአርሲ የሐረርጌ ፣

ለ/ በአዋሳ የካህናት ማሰልጠኛ ፣ የሲዳሞ ፣ የባሌና የጋሞጎፋ

ሐ/ በደበና የካህናት ማሰልጠኛ ፡ የኢሉባቦር ፣ የከፋና የወለጋ

መ/ በባሕር ዳር የካህናት ማሰልጠኛ፡ የጐጃምና የጐንደር ፣

ሠ/ በመቀሌ የካህናት ማሰልጠኛ ፡ የትግራይ የኤርትራና የወሎ ካህናት እንዲሰለጥኑ በመደረጉ ከመላ ጐደል አምስቱም የካህናት ማሰልጠኛ ጣቢያዎች በየዓመቱ በሁለት ጊዜያት የአራት ወራት ኮርስ ይሰጣሉ በዚህም ተመን መሠረት በዓመት አምስት መቶ ካህናት ሲሰለጥኑ በሦስት ዓመታት ፕላን መሠረት አንድ ሺህ አምስት መቶ ካህናትን ለማሰልጠን ታቅዶ ነው ።

ከዚህም በቀር የካህናት የማሰልጠኛ ጣቢያዎች የሥራ ድርሻቸው በየሊቀ ጳጳሳቱ የቅርብ ቁጥጥር ይካሄዳል ። ካህናቱ የሚሰለጥኑባቸው የትምህርት ዓይነቶች ፣

፩ኛ/ ትምህርተ ሃይማኖት ፣
ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ
ለ. ዶግማ
ሐ. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ
መ. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

፪ኛ/ ትምህርተ አበ - ነፍስ
ሀ. የአበ ነፍስነት ተግባር
ለ. የስብከት ዘዴ
ሐ. ሰበካ ጉባዔ
መ. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
ሠ. ሥርዓተ ቅዳሴ
ረ. መዝሙር

፫ኛ/ አስተዳደር ፣
ሀ. ፕላን ፣
ለ. ሠራተኛ
ሐ. አመራር
መ. በጀትና ቁጥጥር

ከገጽ ፩፩ የዞረ

ሠ. ግምገማ
ረ. ማደራጀት
ሰ. ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተ ሰብእ

4ኛ/ ልማት ፡
ሀ. ጤና
ለ. እርሻ
ሐ. ጥበበ - ዕድ
መ. ሂሣብ
ረ. ቋንቋ (ግዕዝና አማርኛ) ናቸው።

፭ኛ/ የካህናት ማሰልጠኛዎቹ ዓላማና ተግባር ፡

እያንዳንዱ የካህናት ማሰልጠኛ ተጠሪነቱ ከፍ ብሎ ከሀ. እስከ ሠ ፊደላት ለተጠቀሱት አህጉራት ሲሆን ፡ ስለዓላማው በተግባር አተረጓጐም ረገድ ፡

፩ኛ/ በስብከተ ወንጌል አቀራረባቸውና በመሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸማቸው ምዕመናንን ወደ ቤተ ክርስቲያን መሳብ እንዲችሉ ፡

፪ኛ/ ለቤተ ክርስቲያናችን ሕልውና ዓይነተኛ ዋስትና ይሆናል ተብሎ የታመነበትን ሰበካ ጉባኤን በየቤተ ክርስቲያኑ እንዲያደራጁ ፡

፫ኛ/ የቤተ ክርስቲያናችን ቅርሳ ቅርሶች የሆኑት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሚጠቀሙ እኳኋን ተዘጋጅተው እንዲጠበቁ ማድረግ ነው ።

፩ኛ/ ከዚህ በላይ በሀ.ሐ.መ.ሠ. ፊደላት የተጠቀሱት ማሰልጠኛዎች በበጀት ረገድ በነፍስ ወከፍ ብር ፱፻፵፰ሺ፰፻

2ኛ/ በለ ፊደል የተጠቀሰው ተመሳሳይ ድርሻ ቢኖረውም እንደአስፈላጊነቱ ብር ፴ሺህ

፫ኛ/ ለካህናቱ ማሰልጠኛዎችና ለሴሚናር ወጭ .... ብር ፳፪ሺ ፰፻፹፪ ብር አንድ ሳንቲም

፬ኛ/ ለማሰልጠኛዎቹ የሂሣብ ምርመራና ለልዩ ልዩ ... ብር ፰ሺ ፱፻፫ .፱ ሳንቲም በድምሩ ብር ፫፻፱ ሺ ፰፻፹፭ ብር ከአሥር ሳንቲም

ድምር ሦስት መቶ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከአሥር ሣንቲም) ይኸውም ሂሣባችን የምንዘጋው በፈረንጆች የቀን አቆጣጠር በመሆኑ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ለአምስቱም የካህናት ማሰልጠኛዎች በየስማቸው የተደረገ የበጀት ክፍያና ሌላም ወጭ መሆኑ አባሪ ቁጥር ፩. የሂሣብ ሠንጠረዥ ያመለክታል ።

እያንዳንዱም የካህናት ማሠልጠኛ ድርሻው ከሆኑት አህጉረ ስብከት ተመርጠው የሚላኩለትን ማለት በቁጥር እስከ ሃምሳ የሚደርሱትን ካህናት እያሰለጠነ፡ ወደመጡበት ሀገረ ስብከት በመመለስ ፡ በሰለጠኑበት የሙያ መስክ በየሰበካዎቻቸው ለሚገኙ ምዕመናን ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን ከመፈጸም ባሻገር ፣ የየክፍሉን የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ የማደራጀት የማጠናከር ትምህርት ለመገብየት እንዲያስችላቸው በዓመት ሁለት ጊዜያት የየአራት ወራት የሥልጠና ሙያ እንዲሳተፉ አምስቱም የካህናት ማሰልጠኛ



በካህናቱ የተተከለው ፓፓዬ
ወደ ገጽ ፩ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# የቂሣርያ ጥያቄ፡

በምድረ እስራኤል ውስጥ ቂሣርያ እየተባሉ የሚጠሩ ሁለት ከተሞች አሉ፡ እነርሱም አንደኛው ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን ምዕራብ ከታላቁ ባሕር ከአ.የጺ አጠገብ ያለው በፍልስጥኤም ወደ.ብ የሚገኝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን ምሥራቅ በአርሞንኤም ተራራ አጠገብ የሚገኝ ፊልጶስ ዘቂሣርያ እየተባለ የሚጠራ ጥንታዊ ከተማ ነው ።

ሁለቱም ከተሞች ስመ አጠራራቸውን በትክክል ለመለየት ሲባል ሁለተኛው ቂሣርያ ፊልጶስ ዘቂሣርያ የሚል የተጸውኦ ድርብ ስም ተሰጥቶታል በሌላ በኩልምይህ ከተማ ፊልጶስ ዘቂሣርያ የሚል ስም የተሰጠው በእነሄሮድስ እያት በፊልጶስ ምክንያት ነው ይባላል ። በዚሁ ስም የእነ ሄሮድስ ዝርያ ሁሉ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ይጠሩበት እንደነበሩ ተረጋግጦአል ። የሄሮድያዳ ባል የሄሮድስ ወንድምም ፊልጶስ ተብሎ የተሰየመው በዚህ ምክንያት እንደ ሆነ ታውቆአል የሄሮድስ የመጀመሪያው ልጁም ፊልጶስ በሚል ስም ሲጠራ እንደነበር ከታሪክ ለመረዳት ተችሎአል ።

ከዚህም ሌላ ፊልጶስ ዘቂሣርያ የሚል ስያሜ ያገኘው ንጉሡ ሄሮድስ የሮምን መንግሥት ለማስደሰት ሲል በገናናው በአውግሥጦስ ቄሣር ስም ቄሣርያ ብሎ እንደሰየ..ው ታሪክ ይናገርለታል ። ከዚህም በላይ ሄሮድስ በፊልጶስ ዘቄሣርያ ከሮም መንግሥት እየተሾሙ የኢየሩሳሌም ገዥዎች ሁነው ይመጡ ለነበሩ መሣፍንት በጣም ያማረ ቤተ መንግሥት ሠርቶ ያኖራቸው እንደነበር በታሪክ ተጽፎአል ። የቄሣር መሣፍንትም አብዛኛው ጊዜአቸውን ያሳልፉ የነበሩ በዚሁ በፊልጶስ ዘቄሣርያ ከተማ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ብቻ ወደ ኢየሩሳሌም እየወጡ ዳኝነት ይመለከቱ እንደነበር ተተርኮአል ።

ፊልጶስ ዘቄሣርያ የአየሩ ባሕርይ በጣም ተስማሚ በመሆኑ ታላላቅ ፈላስፋዎችና ከበርቴ ነጋዴዎችም በብዛት ይኖሩበት ነበር፡ፈሪሃእግዚአብሔርያደረባቸው ጸሎታቸውና ምጽዋታቸውም በእግዚአብሔር ፊት የሠመረላቸው ንዑዳን ክቡራን መኳንንት እንደነበሩበትም ከመጽሐፍ ቅዱስ የነቆርኔሌዎስን ታሪክ ብናነብ ለማወቅና ለመረዳት እንችላለን ። ሐዋርያው ፊልጶስም ለወንጌል አገልግሎት ከዚሁ ሥፍራ እንደ ተጠራና የወንጌል አገልግሎቱን እያካሄደም ትንቢት ይናገሩ ከነበሩ ከአራት ደናግል ሴቶች ልጆች ጋር በፊልጶስ ዘቄሣርያ እንደተቀመጠ እንረዳለን ። (የሐ. ፳፩ ፣ ፰) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ጠላቶቹ ፈሪሳውያን ቅዱስ ወንጌልን በማስተማሩ እንደጥፋት ተቆጥሮበት እንዲከሰስ ካደረጉ በኋላ ተይዞ በዚሁ ከተማ ሁለት ዓመት ሙሉ ታሥሮአል ። በዚሁ ጊዜ ከሁለት ገዥዎች ማለት ከአግሪጳና ከፊስጦስ ፊት ቀርቦ ከጠላቶቹ ጋር ስለታሠረበት ወንጀል እንደተከራከረ ከሐዋርያት ሥራ አንብበን ለማወቅ እንችላለን ። ሐዋርያው በቅዱስ ወንጌል ምክንያት በፊልጶስ ቄሣርያ ከተማ ታስሮ ሁለት ዓመት በተቀመጠበት ጊዜ እስከ ሁለት መቶ የሚደርስ ሕዝብ በዜሁ ሥፍራ ይኖር እንደነበር ከገድለ ሐዋርያት አንብበን ለመረዳት እንችላለን (የሐ.ሥ.፳፫ ፥ ፳፬ ፥ ፳፬ ፥ ፲ ። ፳፭ ፥ ፳፫ ። ፰ ፥ ፵ ፥ ፳፩ ፥ ፰ ። የሐ.ሥ. ፲ ፥ ፩ - ፰ ።)

በፊልጶስ ቄሣርያ የነበሩ ሰዎች የተለያዩ ዜጎች ከመሆናቸውም በላይ የተለያዩ እምነትም ይከተሉ እንደነበር ታውቋል ። ነገር ግን አይሁዳውያንና የአይሁዳውያንን እምነት ይከተሉ የነበሩ ደግሞ በኃያሉ እግዚአብሔር ላይ የነበራቸው እምነት እጅግ በጣም ጽኑ እንደነበር ይተረክላቸዋል ።

ስለዚህ ሐዋርያው ቅ/ ጳውሎስ በአሪት እምነታችን ላይ የማይገባና ትክክል ያልሆነ እምነት አምጥቶአል ። ቤተ መቅደሳችንንም አርክሶአል ከሃይማኖታችን ውጭ የሆኑ አሕዛብንም ወደ ቤተ መቅደሳችን አስገብቶአል ብለው የፈሪሳውያን ጭፍሮች በከሰሱት ጊዜና በዚሁ ከተማም እንደ አንድ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ለፍርድ ሸንጎ በቀረበበት ሰዓት በሃይማኖት ምክንያት ተነቃንቆ የወጣው የከተማው ሕዝብ ለተመልካቹ አስደናቂ እንደነበር የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ተከታታዮች ይናገራሉ ።

የፊልጶስ ቂሣርያ ሌላ ታሪኩ የኢየሩሳሌምን አስተዳደር ከሁለት ክፍሎ የሚወርደው የታላቁ የዮርዳኖስ ወንዝ ምንጩና መነሻው ከዚሁ ከተማ አካባቢ መሆኑን ነው ። እንዲሁም በዚሁ ከተማ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ታላላቅ ተአምራት አሳይቶአል ።

ይኸውም ፩ኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርአብ የባሕርይልጅነቱን በቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነት አረጋግጦበታል ። ፪ኛ/ መለኮታዊ ሥልጣኑን በዚሁ አጠገብ በሚገኘው ተራራ እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጾ አሳይቶአል ። ፫ኛ/ ርኩስ መንፈስ ያደረበትን ልጅ በሥልጣኑ ፈውሶአል ። ( ሉቃ. ፱ ፣ ፲፰ - ፵፭ ።)

ፊልጶስ ዘቂሣርያን በዛሬው ጽሑፋችን ለመጥቀስ የፈለግንበት ዋና ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚሁ ሥፍራ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ያደረገውን ጥያቄና ከደቀ መዛሙርቱ የተሰጠውን መልስ መነሻውንና መድረሻውን ተንትነን ለአንባብያንና ለምእመናን እንድናቀርብ ስለፈለግን ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በብሔረ እስራኤል እየተዘዋወረ ካስተማረባቸው የፍልስጥኤም አውራጃዎች መካከል አንዱ በቄሣርያ እንደነበር ከቅዱስ ወንጌል መረዳት እንችላለን ። ጌታችንም ከገሊላ ተነሥቶ በጢሮስና በሲዶና ዳርቻ አድርጎ ወደፊንቂ ከዚያም ወደ አሦር ከተማ ከአሦር ከተማ ወደ ዳልማኑታ ከዳንግኑታ ወደቤተ ሳይዳ ቀጥሎም ወደፊልጶስ ቄሣርያ እስከገባ ድረስ ልዩ ልዩ ደዌ የያዛቸውን ሁሉ ይፈውሳቸው ነበር ።

ወደዚሁ ከተማ ገብቶም እያሌ ቀናት ተቀምጦአል ። በእነዚህም ቀናት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አንድ ከባድ ጥያቄ አቀርቦላቸዋል ። ጥያቄውም ‘‘ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ነው ይሉታል?’’ የሚል ነበር ። እነርሱም አንዳንድ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎቹ ኤልያስ ፡ ከፊሎቹም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ይላሉ አሉት እርሱም መልሶ ‘‘እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው ፡ ስምዖን ጴጥሮስም አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለው ።

ኢየሱስም ስምዖንን እንዲህ አለው ፡ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ ። በዚህም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ። የገሃነም ደጆች አያናውጿትም ፡ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እስጥሃለሁ ። በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል ።በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል ። ብሎ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶታል ። (ማቴዎስ ፲፮ ፣ ፲፫ - ፲፱ ።)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቄሣርያ ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ ‘‘ሰዎች የሰውን ልጅ ማነው ይሉታል ?’’ ብሎ መጠየቁ ለምን ነበር ? ሰዎች እርሱ ማን ምን እንደሚሉት በባሕርዩ ያውቃል ፣ ነገር ግን በዓለም ላይ የሚኖር ሰው በሚሠራው ሥራ ሁሉ ማጥፋቱንም ሆነ ማልማቱን የሚያውቀው ሰዎች ማን ምን ይሉኛል ? ብሎ ራሱን በራሱ በመጠየቅና ሌሎችንም ጠይቆ ማወቅ እንደሚገባው ይረዳ ዘንድ ለማስገንዘብ ነው ።

በሌላ በኩልም ጌታችን ሰዎች አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ከፊሎቹ ደግሞ ኤልያስ ሳይሆን አይቀርም ጥቂቶቹ ግን ኤርምያስ ይሉታል እንደሚሉት ቢያውቅም ደቀመዛሙርቱም ማን ምን እንደሚሉት ለማወቅ ስለፈለገ ‘‘እናንተስ ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ ጠይቆአቸዋል ። በዚሁ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ’’ ብሎ ሲመልስለት

ይህንንጥያቄእንዲመልስየባሕርይአባቱእግዚአብሔርአብእንደገለጸለትእንጂ ሥጋና ደም ይህን ምሥጢር እንዳልገለጸለት ከነገረው በኋላ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ሰጥቶታል ። ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያቀረበውን ጥያቄ ቅ/ ጴጥሮስ ፈጥኖ ቢመልሰውም ሌሎቹ ደቀ መዛሙርቱ ግን ምን ብለው ለመመለስ ተዘጋጅተው እንደነበር በቅዱስ ወንጌል አልተገለጸም ። ያም ሆነ ይህ ጌታችን መጥምቁ ዮሐንስ ኤልያስ ወይም ኤርምያስ አለመሆኑን ለማስረዳት ከጥያቄው በኋላ በስድስት ቀን ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙ ዮሐንስን ይዞ ወደ ደብረ ታቦር ተራራ ወጣ በዚያም ግርማ መለኮቱን ከመግለጹም በላይ ሙሴ ወይም ኤልያስ ኤርምያስ ወይም መጥምቁ ዮሐንስ አለመሆኑን ለማስረዳት ሙሴን ከመቃብር ኤልያስን ከተሠወረበት ብሔረ ሕያዋን በአካለ ሥጋ አምጥቶ አነጋግሮአቸዋል ።። ሐዋርያትም ሁኔታውን ተመልክተው አምላክነቱንና ከኃሊነቱንም አረጋግጠው ከተራራው ተመልሰዋል ።

ከዚህ ላይ እኛ ልንማረው የሚገባን ሁለት ቁም ነገር አለ ፣ ይኸውም አንደኛ በተሠማራንበት የሥራ መስክ ሁሉ የሚመለከተንን ሥራ ሠርተን ስናበቃ ስለሥራችን ሰዎች ምን ማን ይሉኛል? ብለን እያንዳንዳችን ራሳችንን መጠየቅ እንደሚገባን ፣ ሁለተኛ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን እንጂ እንደ ሕዝበ እስራኤል መጥምቁ ዮሐንስ ? ኤልያስ ? ወይስ ኤርምያስ ከሚለው ኑፋቄ መራቅ እንዳለብን መገንዘብ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች ማን እንደሚሉት ከደቀ መዛሙርቱ ሰምቶ ዝም አላለም ወይም ደግሞ በአምላክነቱ የሚጠራበትን ሁሉ ሰብስቦ መለኮታዊ ሥልጣኑን ለመግለጽ አልወደደም ። ደቀመዛሙርቱን ይዞ ወደተራራው መውጣቱንና አምላክነቱንም ገልጾ ማሳየቱን ግን ስሙን ተሸክመው ወንጌለ መንግሥቱንም ጨብጠው ዓለምን ዞረው ለማስተማር መሄዳቸው ስለማይቀርና ከዚህም ላይ ስደትና መከራ ሊቀበሉ የተጠሩ ስለሆነ በእምነታቸው የጸኑ በሐዋርያነታቸው የታመኑ ሁነው ለመገኘት ይችሉ ዘንድ ነው ። ዛሬም ዓለም የጌታችንን አምላክነት በኑፋቄ ዓይን እንዳይመለከተው አምላክነቱንና ሁሉን ቻይነቱን በትክክል አንድን መሰክረለትና እንድናስተምርለት ያላወቁትንም እንድናሳውቅለት እያንዳንዳችን ለዚሁ የተቀደሰ ተልእኮ ጠርቶናል ።

ስለዚህ አሁንጌታችንመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን ላላወቁ ለማሳወቅ ያልተረዱትን ለማስረዳት ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን ጨብጠን በእውነት ለእውነት ልንነሣ ይገባናል ። ከሁሉ አስቀድመን ግን ሰዎች በሥራችን በኑሮአችንና በጠቅላላ ሁኔታችን ማን ወይም ምን እንደሚሉን ራሳችንን መጠየቅ አለብን ምክንያቱም እውነተኛና ትክክለኛ የሆነ መካሪና አስተማሪ ሰው አስቀድሞ እኔ ማን ነኝ ? ሰዎችስ ስለ ሥራዬ ስለአቋሜስ ምን ይሉኛል ? ብሎ ራሱን በራሱ ጠይቆ ነው ሌላውን አንተ ማን ነህ ? ለምንስ እንዲህ ታደርጋለህ ? ብሎ ለማስተማር የሚችለው በመሆኑም እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ ዓይነቱን ችሎታና ማስተዋል ይሰጠን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ገብረ ክርስቶስ ኃ/ ማርያም





www.ethiopianorthodox.org

# ደብረ ታቦር

ታቦር ወደሚባል ተራራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት ሙሴን ከመቃብር አንሥቶ ኤልያስን ከብሔረ ሕያዋን ጠርቶ ከሐዋርያት ጴጥሮስና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዞአቸው እንደወጣ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 17 በቁ. ፩ ተመዝግቧል ።

ይህ የሆነበት በ፴፪ ዓመተ ምህረት ሲሆን በነሐሴ ወር ቀን ፲፫ ዕለቱ ረቡዕ

መለኮቱን በገለጠ ጊዜ ለምስክርነቱ አቅርቦታል ። ከሐዋርያት ሦስቱን ያመጣበት ምክንያት አለው የፊልጶስ ግዛት በነበረችው ቂሣርያ እኔን ሰው ማን ይለኛል ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ኤልያስ ነው የሚሉህ አሉ ከዚህም ሌላ ከነቢያት ሙሴ ነው የሚሉህ አሉ አሉት ፣ እንም ለሃይማኖትና ለትምህርት እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ትንቢት ተናግሮለታል ።

እንግዲህ ሰዎች ሁሉ ስለ ክርስቶስ በእውነት ከመሰከሩ የክብር ምስጋና ከክርስቶስ እንዲሰጣቸው ይህ ቃል ያስገነዝበናል ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ የባህርይ ልጅ መሆኑ በቅዱስ ጴጥሮስ ምስክርነት ብቻ ተመስክሮ እን



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን መለኮቱን በደብረ ታቦር እንደገለጸ

እንደሆነ ተገልጾአል ። ነቢዩ ሙሴንም ከሙታን አሥንሥቶ ቢርሃነ መለኮቱን ለማሳየት ያመጣበት ምክንያት አለው ቀድሞ በብሉይ ኪዳን ሙሴ ፊትህን ላይ እወዳለሁ ባለው ጊዜ አሁን አልገለጽልህም ግን ኋላ ሰው ሆኜ ሥጋ ለብሼ መሥዋዕት ሆኜ በምቀርብበት ጊዜ በደብረ ታቦር እገለጥልሃለሁ ብሎ ነግሮት ነበርና ጊዜው ሲደርስ እንደመጣ ያስረዳል ።

ኤልያስንም አንተ በኋላ ዘመን ምሥክር ትሆነኛለህ ብሎት ነበርና ብርሃነ ደገና ጥያቄውን ወደ ሐዋርያት መልስ አድርጎ እናንተስ ግን ትሉኛላችሁ ባላቸው ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ የሕያው የእግዚአብሔር አብ የባህርይ ልጅ ነህ ብሎ እውነተኛ የምስክርነት ቃሉን ሰጠ ።

ስለዚህ የዮና ልጅ ጴጥሮስ ሆይ ! ንዑድ ክቡር ነህ በማለት የክብር ምስጋና ሰጥቶታል ። ከዚህም ሌላ የኔን አምላክነት ሥጋዊ እእምሮ አልገለጸልህም ግን ሰማያዊ አባቴ ገለጸልህ እንጂ ካለ በኋላ መሠረት ነህ አለው መሠረትነቱ ደአበቃ አላደረገም።እንደገና ይህ ከተነገረ ከ፯ ቀን በኋላ ፡ ከላይ እንደተገለጠው ከነቢያት ሁለቱን ፡ ከሐዋርያት ሦስቱን ለምስክርነት ወደ ረጅም ተራራ ይዞአቸው ወጣና እጅግ የሚአስፈራ የሚአስደነግጥ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠላቸው ጊዜ ለማየት ሳይችሉ በድንጋጼ ተውጠው ወድቀዋል ። ከደመናውም እንዲህ የሚል ድምፅ ተሰምቶአል ዓለም ሲድንበት የመረጥኩት የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው እሞታለሁ ቢላችሁ አትሞትም አትበሉት ተቀበሉት እንጂ ካለ



በኋላ እግዚአብሔር አብ የባህርይ አባቱ ሲሆን ወልድም የባህርይ ልጅ መሆኑን እንደ መሰከረ ተገልጾአል ።

በሌላ በኩልም መልኩ እንደ ፀሐይ ብሩህ ሆኖአል ። ግን በዓለም ከፀሐይ የበለጠ ብርሃን ባለመኖሩ ከፀሐይ ጋር አነፃፀረው እንጂ ።

ሊቁ አባ ሕርያቆስ ባሕርየ መለኮት ይህን ያህላል ይህነንም ይመስላል ሊሉት አይገባም እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ከበብ የሚወስነው አለ መሆኑን ተናግሯል ። ብርሃነ መለኮት ግን ብርሃናት ሁሉ ሊመሳሰሉት የማይችሉ ከብርሃናት ሁሉ በላይ የሆነ ጽርሐ አርያምና በርባሮስ የማይወስኑት አምላካዊ ብርሃን እንደ መሆኑ ጨለማ አይፈራረቀውም ደመናም ሊጋርደው አይችልም ።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት እነ ሙሴና እነ ጴጥሮስ ፈርተውና ደንግጠው መውደቃቸው ከሚአውቁት ብርሃን በላይ ቢሆንባቸው ነው እንጂ እንደ ፀሐይስ ቢሆን ባልደነገጡም ነበር ።

ግን ብርሃነ መለኮቱ እጅግ የሚአስ ፈ[illegible]ሚአስደነግጥ የመለኮት ኃይልና ግርማ እንደሆነ እንገነዘባለን በዚያን ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ከእሱ ጋር ሲነጋገሩ ተሰምተዋል ። መተርጉማን እንደገለጡት ከነቢያት ሙሴ ነህ ወይም ኤልያስ ነህ እያሉ የሚጠራጠሩት ስለ ነበሩ ሙሴን ክርስቶስ እንዳይሉ ራሱ ሲመሰክር የኔን የሙሴ አምላክ ማነው ሙሴ ነው ያለ አምላክ ሙሴ ይበሉህ እንጂ ሲል መስክሮአል ። ኤልያስንም ክርስቶስ እንዳይደለ የኔን የኤልያስን አምላክ ማነው ኤልያስ ነው ያለ አምላክ ኤልያስ ይበሉህ እንጂ በማለት የባህርይ አምላክነቱን እንደመሰከረ ይተረካል ።

ሐዋርያው ጴጥሮስም በተራራ ላይ ሳለ እጅግ የተራራው ውበት ደስ ስለ አለው ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥያቄ አቀረበ ፤ ቢሆንስ በዚህ ቦታ ሶስት አድራሽ እንስራ አንዱን ላንተ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ በማለት ሀሳቡን ገለጠ ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ መናገሩ የመኖሪያ ቤት ሠርተው በዚያ ለመኖር ሳይሆን ምሳሌውን አውሥቶአል ግን ተራራው የወንጌል ምሳሌ እንደሆነ ተገልጾአል ምሥጢሩም በዘመነ ወንጌል በጴጥሮስ መሠረትነት ቤተ ክርስቲያን እንድትሠራ ተገልጾለት እንደተናገረ ያስገነዝበናል ።

አንዱን ላንተ ማለቱም በክርስቶስ ስም ቤተ ክርስቲያን እንድትሠራ ያስረዳል አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ በማለት ተንትኖ መናገሩ ።ብሉይ ኪዳን በነበሩ ሙሴና ኤልያስ ስም ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ያመለክታል።

ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ ትሕትናው የራሱን ዕድል ፈንታ አልገለጸም ያዕቆብና ዮሐንስንም አልጠቀሰም በዚያን ጊዜ ገና መከራ መስቀልን አልተቀበሉም ነበርና ከመከራቸው አስቀድሞ የክብርን ተስፋ መናገር ተገቢ ባለመሆኑነው በሌላ በኩል ከሐዋርያት ለእነ ጴጥሮስ ብርሃነ መለኮቱን የገለጸላቸው ምክንያት አለው ቀደም ብሎ በ30 ዓመተ ምህረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ አንድነቱን ሶስትነቱን በገለጠ ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስ ብቻ አይቶ ነበረ እንጂ በዚያን ጊዜ ሐዋርያት አልነበሩም ። ምክንያቱም ገና አልመረጣቸውም ነበርና የባህርይ አምላክነቱን በደብረ ታቦር አይተው እስከ አልተረዱ ድረስ ይጠራጠሩ ስለ ነበረ ከጥር ጥር አዘቅት አውጥቶ የባህርይ አምላክነቱን ለማስረዳት ብርሃነ መለኮቱን ገልጾላቸዋል ። ቀደም ሲል ይጠራጠሩ እንደ ነበረ ለመግለጥ ቢአስፈልግ ጴጥሮስ እሞታለሁ ቢለው ይህ ሞት ባንተ ሊደረግ አይገባም ብሎ አስተባብሎ ነበርና የዘብዴዎስ ልጆችም ያዕቆብና ዮሐንስ በምድር የሚነግሥ መስሎአቸው በመንግሥትህ ጊዜ አንዳችን በቀኝህ አንዳችን በግራህ ሹመን ብለው መጠየቃቸው አልቀረም ። ግን የተሰጣቸው መልስ የምትለምኑትን አታውቁምን በማለት ጥያቄአቸው ተደማጭነት አላገኘም ነበር ስለዚህ አምላክነቱን ገልጦ እንዲያምኑበት አድርጓል ።

ከተራራውም ሲወርድ ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ ትእዛዝ ሰጥቶአቸዋል የሚያስተምሩበት ጊዜ ገና አልደረሰም ነበርና ። ሐዋርያት ከጌታ ጋር ሳሉ አላስተማሩም ኋላ ግን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ብሎ የመጨረሻውንም መመሪያ ስለሰጣቸው በዓለም ዞረው እንደ አስተማሩ ታውቆአል ።

እንግዲህ የብርሃን አምላክ ክርስቶስ በዚያን ጊዜ በተራራው ላይ ለነበሩት ለእነ ሙሴ ፣ ለእነጴጥሮስ ብርሃነ መለኮቱን ገልጦ አሳይቶ ከጥርጥር ወደ እምነት ሕይወታቸውን እንደለወጠላቸው ለእኛም ብርሃነ ረድኤቱን ገልጾልን የወንጌልን ቃል እንድናስተምር ልቦናችንን በመንፈሳዊ ዕውቀት ብሩህ ያድርግልን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም እየለ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍቱ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት

የታላቁ ጻድቅ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእ ኀረያ የምትባል ነበረች ሁለቱም በሕግ ተጋብተው ይኖሩ ነበር ። የቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ሠርተው የተራብ በማብላት፣የተጠማ በማጠጣት፣ የታረዘ በማልበስ፣እንግዳን በመቀበል፣ የቅዱስ ሚካኤልን ዝክር በየወሩ በመዘክር፣ይህንና ይህን የመሰለውን በጐ አድራጐት እየሠሩ ልጅ ሳይወልዱ መክነው ይኖሩ ነበር ። ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በአንድ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ዓ.ም. መጋቢት ፳፬ ቀን ጻድቁ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ተፀነሱ በዚህም ሌሊት እግዚእኀረያ በሕልሟ የብርሃን ምሰሶ ከቤቷ ውስጥ ቁሞ የምሰሶው ራስ ከሰማይ ደርሶ በኢትዮጵያ ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በዙሪያው ቆመው ሲማፀኑት ፣ በላዩም ላይ አዕዋፍና ርግቦች ተቀምጠውበት አይታ ለባሏ ጸጋ ዘአብ ነገረችው እርሱም በበኩሉ ከተኛበት አልጋ ሥር ፀሐይ ሲወጣና በዓለም ሁሉ ሲያበራ በሕልሙ አይቶ ለሚስቱ እግዚእ ኀረያ ነገራት ቅዱስ ሚካኤልም ተገልጾ የተመረጠና የተቀደሰ ልጅ ትወልዳላችሁ ብሎ ነገራቸው ከ፱ ወርም በኋላ በ፩ ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ዓ.ም. ከዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ታኅሣሥ ፳፬ ቀን አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ በተወለዱም በሦስተኛው ቀን ፡ ሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፡ ሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ለእግዚአብሔር ምስጋና ሲያቀርቡ እናታቸው ሰምታ በጣም አደነቀች በ፵ ቀናቸውም ጥምቀተ ክርስትናን ሲቀበሉ ፍሥሐ ጽዮን ተብለው ተሰየሙ ፍሥሐ ጽዮንም ማለት የጽዮን ደስታ ማለት ነው ከተወለዱ አንድ ዓመት ከ፫ ወር በኋላ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሙሉ ረሀብ ሆኖ ይልቁንም በእቲሳና በጽላልሽ በዘረሬ ረሀቡ በጣም ስለጸና ጸጋ ዘአብና እግዚእ ኀረያ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል የሚዘክሩበት እጡ ሕፃኑ አባታችን ፍሥሐ ጽዮንም ያለቅሱ ጀመር በጣታቸውም እየጠቀሱ ወደቤት አግቢኝ የማለት ምልክት ስለአሳዩ እናታቸውም ወደቤት ውስጥ ታቅፋ ይዛቸው ገባች በዚያም አንድ ድርጐ የሚሆን በዕንቅብ ትንሽ ስንዴ ነበርና ሕፃኑ አባታችን አምጪ እያሉ ያመለክቱ ጀመር እናታቸውም ዕንቅቡን አቀረበችላቸው በእጃቸው ስንዴውን ቆንጥረው ቢመልሱት ዕንቅቡን ሞልቶ ተረፈ ከዚያም ሌላ ዕንቅብ ብታቀርብ እህል በየዓይነቱ ሞላ በዚህ ምልክት የልጇ እጅ በረከት አልችበት ብላ የቅቤውን ማሠሮ የጨውን የቅመማ ቅመሙን ዕቃ ብታቀርበው የሕፃኑ እጅ ያረፈበትና የነካው ዕቃ ሁሉ በየአይነቱ ሞልቶ ተረፈ ይህንም ላደረገላት ለፈጣሪዋ ክርስቶስ የጠለቀ ምስጋና አቀረበች ሊታጐልባቸው የነበረውንም የቅ/ሚካኤልን ዝክር አዘጋጅታ ካህናትንና ድሆችን ጠርተው አበሉ አጠጡ በዚህም ሁናቴ ሕፃኑ ፍሥሐ ጽዮን አድገው ፯ ዓመት ሲሆናቸው ከአባታቸው ከጸጋ ዘአብ ንባብና ዳዊት ቅዳሴ ከቃል ትምህርት ጋር አጠናቀው እንደተማሩ ከአባ ጌርሎስ ዘንድ ዲቁና ተቀብለው እየቀደሱ ቀሪ ትምህርታቸውን የብሉይና የሐዲስ ትርጓሜን አጠናቀው ተማሩ ከዚህ በኋላ ወደ አማራ ሳይንት ሄደው የቅስና ማዕርግ ከአባ ጌርሎስዘንድ ተቀብለው ሲመለሱ ጳጳሱ ሐዲስሐዋርያ ትሆናለህ በመላም ሀገረ ስብከት ሊቀ ካህናት ሁነህ እንድትሠራ ሹሚሃለሁ ብለው መርቀው ላኳቸው ፍሥሐ ጽዮንም እየተዘዋወሩ የወንጌልን ትምህርት በማስተማር ላይ ሳሉ እናታቸው እግዚእ ኀረያ ነሐሴ ፲፪ ቀን አረፈች በተከታታይም አባታቸው ጸጋ ዘአብ ነሐሴ ፲፯ ቀን አረፈ አባታችን ፍሥሐ ጽዮንም ከጥቂት ቀን በኋላ ከኀዘናቸው ተጽናኑና አቋርጠውት የነበረውን የወንጌል ትምህርት ቀጠሉ ።

ከዕለታት አንድ ቀን መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ የእግዚአብሔር ባለሟል ፍሥሐ ጽዮን ሆይ እነሆ እግዚአብሔር ድውያንን የመፈወስ አጋንንትን የማባረር ሙታንን የማንሣት ድንቁርናን የማጥፋት የጣዖታትን ቤት የማፍረስ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን የመሾም የወንጌል ትምህርትን የማስተማር ሥልጣን ከአምላክ ተሰጥቶሃልና ከዛሬ ጀምሮ የፊተኛው ስምህ ተለውጦ ስምህ ተክለ ሃይማኖት ይባላል አላቸው ከዚያም በኋላ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የወንጌልን ቃል ማስተማር ጀመሩ በመጀመሪያ ቻይ የምትባለውን ወንዝ ተሻግረው በከተታና በፈጠጋር በዳሞትና በቢለት በውራጌ ወረዳ እያስተማሩ ወላይታ ደርሰው የወንጌልን ትምህርት ያስተምሩ ጀመር በዚህም በወላይታ መተሎሚ የሚባል ከሐዲ ተነሥቶ በሸዋና በዳሞት በውጋዴንና በአርሲ እስከ አማራ ሳይንት ወሰን ድረስ ብዙ ጥፋት እያጠፉና ጣዖትም በማቆምና ለጣዖት በማሳገድ የክርስቲያን ሃይማኖት ጠላት ሁኖ ብዙ ዘመን የኖረውን ከሐዲ ሳይፈሩ ከከተማው ገብተው የወንጌልን ስብከት ሲሰብኩ ከሐዲ[illegible]ንጉሥ መተሎሚ ተቆጥቶ በጻድቁ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ላይ ብዙ መከራና ሥቃይ አድርሶባቸዋል ። ቢሆንም በክርስቶስ ረድኤት በሚያስደንቅ ሁናቴ ከሞት ድነው ልዩ ልዩ ተአምራት በማድረግ ቀርበው ንጉሡን አሳፈሩት ። በሁኔታቸውም ተገርሞ በጻድቁ እጅ ከነሠራዊቱ አምኖ ተጠምቆላቸዋል ። ከእብደቱም አድነውታል ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ይህን ታላቅ ጸጋ ከአምላካቸው ስላገኙ በጣም ተደስተዋል ።

ይህንን ላደረገላቸው አምላክ ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ወደአማራ ሳይንት ሔደው ከግሸኑ አባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ገብተው በአበ ምኔቱ በአባ በጸሎተ ሚካኤል ፈቃድ የሥርዓተ ምንኩስና ትምህርት ይማሩ ጀመር በዚያም በነበሩበት ጊዜ በቀን ሦስት ሦስት ቅርጫት በሌሊትም እንዲሁ ሦስት ሦስት ቅርጫት እህል ለመነኮሳቱ ምግብ በመፍጨት በአንድ ጊዜ ሁለት እንስራ ውሃ በመ



ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲጸልዩ'



www.ethiopianorthodox.org

ቅዳት በየዕለቱ ፵ ፵ ሽክም እንጨት በመፍለጥና እርሻ በማረስ ደካሞችን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ በማገልገል ይህንና ይህን የመሰለውን ትሩፋት በመሥራት ፲ ዓመት ካገለገሉ በኋላ ከዚያ ተሰናብተው በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ደሴት ሄደ ዋል ከዚያም ከጻድቁ ከኢየሱስ ሞዓ ጋር ተገናኝተው በገዳሙ ተግባር ቤት ውስጥ ተመድበው ከ፲ ዓመት በላይ በማገልገላቸው ተመርቀው ለአገለገሉ መነኮሳት ሊሰጥ የሚገባውን ልብስ ከ አበ ምኔቱ ከኢየሱስ ሞዓ ዘንድ ተቀብ ለው ከገዳሙ በመሰናበት በትእዛዘ እግዚአብሔር ወደደብረ ዳሞ ገዳም ፡ ሔደዋል በዚያም ከአበ ምኔቱ ከአባ ዮሐኒ ዘንድ ተገናኙ ከዚያም ተሰናብ ተው ለገዳማውያኑ መውጫና መው ረጃ እንዲሆን በተዘጋጀው ገመድ ሲወ ርዱ መነኮሳቱ ሲሸኙአቸው ከገደሉ አፋፍ ላይ እንደቆሙ ገመዱ ከካስማው አጠገብ ተበጥሶ መነኮሳቱም ደንግጠ ው እንደቆሙ ከመ ቅጽበቱ ዓይን ፮ ክ ንፍ አውጥተው በክንፈ ጸጋ ሲበሩ መነ ኮሳቱ በዓይናቸው አይተው እጅግ በጣ ም አድንቀዋል ።

ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም እየ ተዘዋወሩ እንዲያስተምሩ እግዚአብሔ ር ስለአዘዛቸው በእኩስምና በአው ዜን በፀዓዳ ዓንባና በጉንዳጉንዶ ከዚ ያም ወደዋሊ ሔደው ከቅዱሳን ጋር ተ ገናኝተው የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ ተወያይተዋል ። በዋልድባም ከደ ጋጉ አበው መነኮሳት ጋር ከተገናኙ በ ኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ከእስክንድርያ ው ሊቀ ጳጳሳት አባ ሚካኤል ጋር ተገና ኝተው በመባረክ ወደ ግብፅ ተመል ሰው ገዳመ አስቄጥስንና ገዳመ ሲሐ ትን ወዘተ ጉብኝተው ወደ ሀገራ ቸው ኢትዮጵያ ተመልሰው እንደተለ መደው እየተዘዋወሩ የወንጌልን ቃል በሰፊው አስተምረዋል ።

ከዚያም በላስታ ሮሃ የሚገኙትን የቋ ጥኝ አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተው ና ባርከው እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ኢየ ሩሳሌም ሔደው በመሳለም ተመልሰ ዋል ።

ከዚህ በኋላ ጠቅላላ የኢትዮጵያን ምድር እየተዘዋወሩ በመባረክና ትምህ ርት በመስጠት አብያተ ጣዖታት እንዲ ዘጉ አብያተ ክርስቲያናት በብዛት እን ዲታነፁ አድርገዋል ። ቀሳውስትንና ዲያቆናትንም ሾመዋል ።

በመጨረሻም በ፲፱ቱ ሐዋርያትና በ ፸፱ቱ አርድእት አምሳል ያስተማሩአ ቸውን ደቀ መዛሙርት በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየዞሩ እንዲያስተምሩ ከሾሙ በኋላ በሸዋ ክፍለ ሀገር ሰላሌ አውራጃ ውስጥ ደብረ ሊባኖስ የሚባ ለውን ገዳም አቋቋሙ ፤ በዚሁም በደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አጠገብ ደብረ አስ ቦ በተባለው ዋሻ ግራ ቀኝ ሁለት ቋሚ እንጨት አቁመው እንደሾህ የሚወጋ ሦስት ሦስት ጦር ያለው ብረት አስቸን ክረው በመካከሉ ላይ ቆመው ሳይቀመ ጡ በጾም በጸሎት በስግደት ተወስነው ፲፰ ዓመት ሙሉ ፀሐይ ሳያዩ እንደቆሙ ከቁመታቸውም ጽንዓት የተነሣ ጥር ፳፬ ቀን አንድ እግራቸው ተቆርጣ ወደ ቀች ። ይህንንም መጽሐፍ ገድላቸው ይናገራል ።

ከዚያም በማያያዝ የሥጋን ሥቃይና ድካም ባለመሰቀቅ ሳይሰለቹ እንደገና ባንድ እግራቸው ሰባት ዓመት ቁመው ጸልየዋል በመጨረሻም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከድንግል ማ ያምና ከወዳጆቹ ቅዱሳን ጋር ተገልጾ ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ሆይ ጾምህንና ጸሎትህን ተቀብየሃለሁ በምድር ላይ ስምህን ጠርቶ በስምህ የሚለምነኝን ሰው ፈጥኜ እሰማዋለሁ በስምህ ዝክርህ ን የሚዘክረውን ምጽዋት የሚሰጠውን ስእለት የሚያቀርበውን በስምህ መከ ራ የሚቀበለውን አንተ ከገባህበት ውሳ ጤ መንጠላዕት አስገባዋለሁ አንተ ከደ ከምክበት ገዳም ለመጸለይና ለመስገድ የሚመጣውን ሁሉ ልመናውን እሰማዋ ለሁ ብሎ ነገራቸውና ታላቁ ጻድቅ አቡ ነ ተክለ ሃይማኖት በአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ ዓ ም ነሐሴ ፳፬ ቀን አር ፈው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ውስጥ ደብ ረ አስቦ በሚባል ዋሻ በክብር ተቀበሩ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ታላቅ ጻድቅ የቅድስና ሥራ ተመልክታ ገድል ጽፋ ቅዱስ የሚያሰኘውን ስም ሰጥታ የተወለዱበትን ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ያረፉ በትን ነሐሴ ፳፬ ቀን በየዓመቱ በከፍ ተኛ ሥነ መርዓት ታከብረዋለች ።

አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ

## ዜና .......

ከገጽ ፳፩ የዞረ

አዝማዶች ወዳጆች በተገኙበት የቀብ ሯ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሟል ።

በዚህም ወቅት አብሮ አደግ የሆኑት መንፈሳዊ ጓደኞቿ በቦታው ባይገኙም የነሱ ወንድሞች የሆኑት የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ምክሃ ደናግል ማርያ ም የሰንበት ት/ቤት አባላት ተገኝተው በመካነ ቀብሩ ላይ የሃዘን መግለጫ አ በባ አድርገዋል ።

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደመሰከሩት ‘‘የጻድቃን ሞታቸው እረፍታቸው’’ ነው እንዲሉ የዚች ጉብል ወጣት እረፍ ት የሚያሳዝነን ለሷ ሳይሆን ለሁላችን የማይቀርልን የመጨረሻ ጽዋችን ስለ ሆነ እኛ ክብራችን ጐድፎ ኃጢአትን በማብዛት ፈጣሪያችንን አስቀይመነው የሰጠን የክብር ዕቃ ሆነን ኃጢአታችን በንስሐ ሳናጥበው መልአከ ሞት መጥ ቶ እንዳይጠራን ኃዘናችን ለራሳችንም ነው ።

እሷንስ አንች ክብርት ነፍስ በምድር ላይ በጾም በጸሎት ተወስነሺ መልካም ከመሥራት በስተቀር ማንንም ሳታስቀ ይሚ ደስ እንዳሰኘሺኝ ነይ እኔ ደስ አሠ ኛሻለሁ ብሎ ክብርት ነፍሷን በአብርሃ ም ዕቅፍ እንደሚያኖራት የፈጣሪአች ንን ቸርነት አንጠራጠርም ።

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል



# ዜና ሊቃውንት

በዛሬው ጽሑፋችን ለአንባብያን የ ምናቀርበው በሕይወተ ሥጋ በማስተ ማር ላይ ከሚገኙት ሊቃውንት ስለ አለቃ ይሄይስ ኪዳነ ማርያም አጭር የሕይወት ታሪክ ይሆናል ።

አለቃ ይኄይስ ኪዳነ ማርያም ከአባታ ቸው አቶ ኪዳነ ማርያም ከእናታቸው ወ/ሮ ይሻሙ አድገህ በ1909 ዓ.ም. በጐንደር ሀ/ስብከት በደብረ ታቦር አ ውራጃ በእስቴ ወረዳ እንዳቤት ልዩ ስሙ ጐጣ ኪዳነ ምህረት ከሚባል ደብ ር ተወለዱ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከዚያው ከተወለዱበት ደብር ከነበሩት አባ አድገህ ከተባሉት መም ህር ትምህርት ጀምረው ከፊደል እስከ ጾመ ድጓ ድረስ ተምረዋል ።

ከዚያም በፎገራ ወረዳ ወደምትገኘ ው ክርስቶስ ሠምራ ሄደው አባ ኪሮስ ከ ሚባሉት መምህር ጽዋትወዜማን ተምረ ዋል ቀጥሎም እስቴ ወረዳ አጋጥ ጽዮን ከመሪጌታ ሙጩ ላቀው ሂደው ድጓ በሚገባ አጣርተው ከተማሩ በኋላ እንዳቤት ደረባ መርቆሬዎስ ከመሪጌታ እሸቴ ቅኔ ተምረው ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀኝተው ሲያበቁ ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ደብረ ዕንቁ ማርያም ከመ ምህር ጌጡ ተሰማ የቅኔ ትምህርታቸው ን በማጠናከር አገባቡን ከእነአርባ ቅም ሩ ከማጥናታቸውም ሌላ የውዳሴ ማር ያምንና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ ተ ምረው ወደ መሪጌታ ሙጩ ላቀው በመመለስ የድጓ ትምህርታቸውን ቀጥ ለዋል ።

ከዚያም የድጓውን ዜማ በሚገባ አጥ ንተው ከጸፉ በኋላ በ1937 ዓ.ም. ድጓ ለማስመስከር ጋይንት አውራጃ ወደም ትገኘው ቤተ ልሔም ሄደው ድጓውን አስመስክረው በ1939 ዓ.ም. ተመር ቀው ምክሬ ሐና ከተባለችው ቤተ ክር ስቲያን 5 ዓመታት አስተምረዋል ከአ ምስት ዓመታት በኋላ ወደተወለዱበት ደብር ጐጣ ኪዳነ ምሕረት ሂደው ከ19 44 እስከ ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. ድረስ አስተም ረዋል ። ከ፲፱፻፸፩’ዓ.ም. ወዲህ ደግሞ በብፁዕ አቡነ መርቆሪዎስ ፈቃድ በቅ ሎ ፍለጋ ኪዳነ ምሕረት ወደ ተባለችው ደብር ሂደው ቤተ ክርስቲያኑን በማኅ ሌት ምእመናኑን በስብከተ ወንጌል በማገልገል ላይ ይገኛሉ ።



አለቃ ይሄይስ ኪዳነ ማርያም

አለቃ ይሄይስ ኪዳነ ማርያም ወንበር ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ 37 ዓመ ት ሲሆናቸው ከእርሳቸው እየተማሩ ድጓ ያስመሰከሩና ድጓ ተምረው ለማ ስመስከር በዝግጅት የሚገኙ በከፊል የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ መሪጌታ ቀለመ ወርቅ ተገኝ
፪ኛ/ » ሐዋዝ ካሣሁን
፫ኛ/ » ክንፈ ርግብ አታለል
፬ኛ/ » አስረግዳ እምባው
፭ኛ/ » መኮንን በቃ
፮ኛ/ » መልአኩ ወርቅነህ
፯ኛ/ » ይግዛው የሺታ
፰ኛ/ » ልብሰ ወርቅ ደርሶ
፱ኛ/ » ማርቆስ ይግዛው
፲ኛ/ » ዘለዓለም መንግሥቱ
፲፩ኛ/ » መዘመር
፲፪ኛ/ » መሪጌታ ኤፍሬም
፲፫ኛ/ » ኃይለ ልዑል
፲፬ኛ/ » በጽሐ ሰንደቁ
፲፭ኛ/ » ጀንበሩ ጥሩነህ
፲፮ኛ/ » ውቤ ተሰማ ወዘተ ሲሆኑ ስማቸውም ያልተጠቀሱ ብዙዎች ና ቸው ከአለቃ ይኄይስ ኪዳነ ማርያም እየተማሩ በቅስና በዲቁና በመዘምር ነት ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት ስፍር ቁጥር የላቸውም ።

አለቃ ይኄይስ ቤተ ክርስቲያንን ለ ማገልገልና ለማስተማር የነቁና የተጉ በመሆናቸው አሁንም እንደንብ ከበው ሌት ከቀን መንፈሳዊ ትምህርታቸውን የሚመገቡ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ቁጥ ራቸው እጅግ በጣም በርከት ያለ ነው ።

አለቃ ይኄይስ ‘‘በጸጋ ዘነሣእከሙ በጸጋ ሀቡ’’ የሚለውን ቃለ ወንጌል በመከተል ብዙ ደቀ መዛሙርቶችን አስተምረው አሠልጥነው ለቤተ ክርስ ቲያን አገልግሎት ያቀረቡና የሚያቀር ቡ ታላቅ ሊቅ ናቸው እርሳቸውም ሆኑ እርሳቸውን የመሰሉ ምሁራን ሁሉ ደቀ መዛሙርትን ከማስተማር ቤተ ክርስቲ ያንንም ከማገልገል እንዳይቦዝኑ በዚ ህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንፈልጋለን።

የጐንደር ሀ/ስብከት ጽ/ቤት



www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

## ቅድስት እንባመሪና

አዘጋጅ ብርሃኑ ተድላ

እንባመሪና ከአንድ ክርስቲያናዊ ባለጸጋ ሰው የተገኘች ስትሆን የመፈልሞሪያ ስሟም ማርያም እንደነበርና ይህችም ልጅ ገና በሕፃንነቷ ወራት እናቷ በሞት ስለተለየቻት አባቷ ብቻውን በትምህርትና በመልካም አስተዳደግ እንዳሳደጋት የቤት ክርስቲያናችን የታሪክ መድበል የሆነው ስንክሳር ያስረዳል ።

ይኸው መጽሐፍ ስለ ቅድስት እንባመሪና ሲያብራራ እንዲህ ይላል ። እንባመሪና ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ አባቷ ልጁን ትዳር አስይዞ እርሱ ሊመለኩስ አስበ ሃሳቡም ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሄዶ ሊመለኩስ ነበርና ሃሳቡን ለልጁ ለማርያም አካፈላት ይላል ። ማርያምም የአባቷን ሃሳብ ከሰማች በኋላ አባቷን እንዲህ አለችው አባቴ ሆይ ሃሳብህ መልካም ነው ቢሆንም አንተ ነፍስህን ስታድን ለመሆኑ የኔ ነፍስ እንድትጠፋ ታስባለህን ? ስትል ጠየቀችው አባቷም ልጄ ሆይ እኔ ምን ላድርግ ብለሽ ነው ወደ ገዳሙ ይገፍሽ እንዳልሄድ አንቺ ሴት ነሽ እዚህም ብቻሽን እንዳልተውሽ ማን ይረዳሻል በሕግ መኖሩ መልካም ነው ብዩ ነው አላት እርሷም አባቴ ሆይ ችግርህ ይህ ከሆነ የሴቶችን ቀሚስ ላውልቀውና የወንዶችን ልብስ አልብሰኝ አለችው ሀዲያውኑም ፀጉሯን ተላጭታ የወንዶችን ልብስ ለብሳች በተጋድሎ ለመኖርም ፈቷ ጨክና በደንብም ተዘጋጀች አባቷም ያለውን ገንዘቡን ለነዳያን መጽውቶ ጨረሰ በመጨረሻም የልጁን የማርያምን ስም እንባመሪና ብሎ ሰወጣላት ሲታውንቴ እንደሚሉት እንባመሪና ማለት መናኝ ማለት ነው ሲሉ ይተረጉሙታል እንባመሪና አባቷም አብረው ወደ ገዳመ አስቄጥስ ሄደው ከገዳሙ ውስጥ አብረው በምንኩስና ለአሥር ዓመታት ያህል በጾም በጸሎት ተወስነው በገዳሙ ሙእየረዱ ኑረዋል ይላል መጽሐፉ ።

መጽሐፉ ታሪኩን በማብራራት የእንባመሪና አባት ከአሥር ዓመት በኋላ በሰላም ማረፉን ይናገርና እንባመሪና ብቻዋን በዚያው ገዳም ውስጥ በጾም በጸሎት ተወስና ኖረች ። በዚህ ሁኔታ ስትኖር የገዳሙ አበምኔት ሦስት መነኮሳትና አባ እንባመሪናን ጨምሮ ለገዳሙ መነኮሳት ምግብ እንዲያመጡ ወደ ሌላ ሀገር ላካቸው ምክንያቱም አበምኔቱም ሆነ ሌሎች መነኮሳት አባ እንባ መሪና ወንድ እንጂ ሴት መሆኗን አያውቁም ነበርና ነው ። እንባመሪናም ከመነኮሳቱ ጋር ሲሄዱ ስለመሸባቸው ከአንድ ነጋዴ ቤት አደሩ ።

በዚህን ጊዜ መነኮሳቱ በእንግድነት በአደሩበት ቤት የነጋዴው ሴት ልጅ ነበረችና ሌሊት አንድ ጐረምሳ ገብቶ ክብረ ንጽሕናዋን ከደፈረ በኋላ አባት ሽ ክብረ ንጽሕናሽን የወሰደው ማነው ብሎ ? ቢጠይቅሽ በእንግድነት ከአደሩት መነኩሳት መካከል አንዱ አባ እንባመሪና ነው በይ ብሏት ሄደ፡ ከጊዜ በኋላም አባቷ ልጁ እንደ ፀነሰች አውቆ እንዲህ ሲል ጠየቃት ልጄ ምን ሆንሽ ክብረ ንጽሕናሽንስ ያጠፋብሽ ማነው ? አላት እርሷም አባቴ ሆይ አባ እንባመሪና የተባለ መነኩሴ ነው አለችው አባቷም ተናዶ ወደ ገዳሙ ሄዶ መነኩሳቱን ይራገምና ይሰድብ ጀመር። የነጋዴውን ጩኸትና ስድብ የሰሙት የገዳሙ አበምኔት ወጥተው ለምንድነው ወደ ገዳሙ ገብተህ የምትጮኸውና የምትሳደበው ለመሆኑ ሌላውስ ይቅር የፈጠረህን አምላክህን አትፈራምን? በማለት ጠየቁት እርሱም በእንግድነት ከእርሱ ቤት ያሳደራቸው መነኩሳት በልጁ ላይ የፈፀሙትን ነገር በተለይም አባ እንባመሪና የተባለው መነኩሴ የሠራውንሥራ ዘርዝሮናተንትኖ አስረዳው የገዳሙም አበምኔት እጅግ አዘኑ ያንንም ነጋዴ ይህንን ወሬ እንዳይናገርና ወሬውም በሰዎች ዘንድ እንዳይሰራጭ ለመኑውና ሸኘው ።

እንደ ገና አበምኔቱ አባ እንባመሪናን ጠርቶ ተቆጣው በጣምም ገሠፀው አባ እንባ መሪና ግን ይህ ሁሉ ስድብ ከአበምኔቱ ሲደርስበት ስለምን እንደ ሆነ የተረዳው ነገር ስላልነበረ ነገሩን ለመረዳት ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ርግማን የምትረግመኝ በምን ምክንያት ነው ምንሳ አጥፍቼ ነው? በማለት ጠየቀው የገዳሙም አስተዳዳሪ በእንግድነት ካደሩበት ቤት የማይገባ ሥራ እንደሠራና በዚህም እንደተከሰሰ ነገረው አባ እንባመሪናም ይህንን ከሰማ በኋላ እኔ ጐበዝ ስለሆንኩ አዎን ተሳስቻለሁ ይቅር በለኝ ኃጢአቴንም አሥተሥርይልኝ አለችው በዚህ ጊዜ አበምኔቱ እጅግ ተናደደና ከገዳሙ እንዲወጣ አደረገው ።

አባ እንባመሪናም የነጋዴው ልጅ እስትትወልድ ድረስ ከገዳሙ ውጭ ይኖር ነበር ። የነጋዴው ልጅ እንደወለደች ሕፃኑን አምጥተው ለአባ እንባ መሪና ሰጡት እንባ መሪናም ሕፃኑን በደስታ ተቀበሉ ላሞች በዋሉበት እየዞረ እረኞቹን ወተት እየለመነ ሕፃኑን ያጠባው ነበር ይላል መጽሐፉ ።

ምንም እንኳ ይህ ሁሉ በደልና ችግር በአባ እንባመሪና ላይ ቢደርስም በጾም በጸሎት በተጋድሎ ሦስት ዓመት ያህል ከገዳሙ ውጭ ከኖረ በኋላ የገዳሙ መነኮሳት ሁሉ ተሰብስበው አበምኔቱን አባ እንባመሪና ወደ ገዳሙ ይመለስ ዘንድ ይቅር በለው በማለት ለመኑት አበምኔቱም ልመናቸውን ተቀበሉ ክበድ ያለ ቀኖና ሰጥቶ ወደ ገዳሙ እንዲገባ አደረገ ። አባ እንባመሪና ወደ ገዳሙ ተመልሶ ከገባ በኋላ ወጥ እየሠራ ቤት እየጠረገ ውሃ እየቀዳ ሲኖር ሕፃኑም አድጐ ለምንኩስና ስለደረሰ መነኮሰ አባ እንባመሪናም ፬ (አርባ) ዓመት በዚያ ገዳም ኖሮ ሦስት ቀን ታሞ ነሐሴ 15 ቀን አረፈ ይላል ስንክሳር ።

ታሪኩን በመቀጠል የገዳሙ አበምኔትም የአባ እንባመሪናን እረፍት ሰምቶ መነኩሳቱን ሰብስቦ ሊገንዙት ልብሱን ቢገልጡ ሴት ሆና አገኟት ። በዚህ ጊዜ መነኮሳቱ በመደናገጥ አቤቱ ማረን አሉ ። ይህንንም ድንቅ ሥራ በማየታቸው በታላቅ አድናቆት ለአበሜኔቱ ነገሩት እርሱም ስለተናገራት ኃይለ ቃል በእርሷ ላይ በደረሰው በደል ሁሉ እየተጸጸተ በታላቅ አድናቆት አለቀሰ ከዚህ በኋላ አበምኔቱ የነጋዴው ልጅ ከአባ እንባመሪና እንዳልወለደች ለማስረዳት ወደ ነጋዴው ቤት መልእክተኞችን ላከ ። እንባመሪናም ሴት መሆኗን መልእክተኞቹ ለነጋዴው አስረዱት ።

በመጨረሻም አበምኔቱና መነኮሳቱ በመሆን በብዙ ልቅሶ ገንዘው በዝማሬና በማህሌት ቀበሯት ያችን የነጋዴውን ልጅ ክብረ ንጽሕና የደፈረው ጐረምሳና የነጋዴው ልጅ ጭምር ጸላኤ ሠናያት አድሮባቸው ብዙ ያሠቃያቸው ነበር ሌላው ቀርቶ እንባመሪና ወደተቀበረችበት ቦታ እየወሰደ ያስጮኻቸው ነበር ይላል ። ሁለቱ የፈጸሙትንም በደል ገልጠው ይናገሩ ነበር ።

እንግዲህ ከዚህች ቅድስት ሴት የምንማረው በመጀመሪያ አባቷ ለምናኔ ሲዘጋጅ አንተ ነፍስህን ስታድን የእኔ ነፍስ እንዴት ትጥፋ ብላ በቆራጥነት ተናግራ ከአባቷ ጋር መመነኗ ከገዳሙ ከገባች በኋላም በምንኩስና ተወስና ፆታዋን ሳትገልጽ ለተሰለፈችበት ዓላማ በጾምና በጸሎት መቆየቷ ሲሆን ከአባቷ ሞት በኋላ ዓላማዋን ሳትለውጥ ስትኖር ከላይ እንደተገለፀው ባልሠራችው ስራ ስትወቀስ ስትከሰስ አልፎም ስትወገዝ ወንድ አለመሆኗን ገልጸ ማሳፈር ስትችል በትእግሥት ተወቀሰች "ትእግሥት መራራ ናት ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው" እንደተባለው ሁሉ ሁሉንም በትእግሥት ያሳለፈችው እና ባመሪና በመጨረሻ የትእግሥትን ፍሬ አገኘች ወቃሾችና ከሳሾቿም አፈሩ ተፀፀቱ እርሷም ለታላቅ ማዕርግ ደረሰች በሴትነቷ ከአባቷ እንዳትለይ የወንድ ልብስ በመልበስ ካሰበችበት ቦታና ማዕርግ ደረሰች ለጥሩ ሥራ በጥሩ መንፈስ ለተነሣ ሁሉ ረዳቱ እግዚአብሔር ነውና ከፍጻሜ ያደርሰዋል ።

እንግዲህ አንድ ሰው አንድን ሥራ ለመሥራት ዋናው ፍላጐት ነው ፍላጐት ካለ ምንም ሊያግደው እንደማይችል እንረዳለን ።

ስለዚህ እኛም የቅድስት እንባመሪናን አርአያ በመከተል የሚደርስብንን ፈተና ሁሉ በትእግሥት በማሳለፍ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ያብቃን ።

ወ/ሮ ብርሃን ተድላ

## ልደተ ሙሴ

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በ፲፻፫፻፯፻፬፻ ዓ.ም ተወለደ አባቱ እንበረም እናቱ ዮካብድ ትባላለች ሙሴ በተወለደበት ዘመን እስራኤላውያን በግብፅ በፈርዖን ትእዛዝ እጅግ ፅኑዕ አስከፊ ስቃይ በበዛበት አገዛዝ ሥር ወድቀው ነበር ግብፃውያን እስራኤላውያንን በመከራ ከሚገዙአቸውም ሌላ በፅኑዕ ሥራም ያስመርሩአቸው ነበር።ከዚያም በተጨማሪ የግብፅ ፈርዖን ሲፓራና ፎሐ የሚባሉትን የዕብራውያንን አዋላጆች እንዲህ አላቸው የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ ወንድ ቢወለድ ግደሉት ሴት ብትወለድ በሕይወት ትኑር የሚል ትእዛዝ ሰጣቸው ።

አዋላጆቹ ግን እግዚአብሔርን ፈሩ የግብፅ ንጉሥ እንዳዘዛቸው አላደረጉም ወንድ ሲወለድ አልገደሉም በዚህ ጊዜ ነው ንጉሡ ትእዛዙን እንዳላከበሩለት ባየ ጊዜ አዋላጆቹን አስጠርቶ ለምን ትእዛዜን አልፈጸማችሁም ወንዶች ልጆችን ለምን አልገደላችሁም ቢላቸው አዋላጆቹም ለንጉሡ መልሰው የዕብራውያን ሴቶች እንደግብፅ ሴቶች ስለአልሆኑ እነሱ ጠንካሮች ናቸውና አዋላጆች ሳይገቡ ስለሚወልዱ ነው አሉት ፈርዖንም መልሶ ይህ ከሆነ የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ወደወንዝ እንዲጣል የሚል ትእዛዝ ሰጠ ።

ይህ አዋጅ በታወጀበት ጊዜ ነው ሙሴ የተወለደው ሙሴ በተወለደ ጊዜ እናቱ በጣም አዘነች ሦስት ወርም ሸሸገችው ከዚህ በኋላ ለመሸሸግ ባልቻለች ጊዜ የደንገል ሣጥን በልኩ ሠርታ በዚያ ውስጥ በማድረግ በወንዝ ዳር ባለ በቄጤማ ውስጥ አስቀመጠችው እህቱም በሩቅ ቆማ ከሚደርስበት ነገር ሁሉ ትጠብቀው ነበር ።

በዚያም ቦታ የንጉሡ የፈርዖን ልጅ ቴርሙስ ወለተፈርዖን ሰውነቷን ልትታጠብ ደንገጡሮዋን አስከትላ ወደዚህ መጣች በወንዙም ዳር ስትዘዋወር ሣጥኑን በቄጤማ ውስጥ አገኘች ደንገጥርዋንም ልካ አስመጣችው ደንገሉም በተከፈተ ጊዜ ሕፃኑን አየች ሕፃኑም ያለቅስ ነበር አዘነችለት እርሷም ይህ ከዕብራውያን ልጆች አንዱ ነው አለች ሕፃኑን አየች ሕፃኑን ትጠብቅ የነበረች እህቱ ለፈርዖን ልጅ ሕፃኑን ታጠባልሽ ዘንድ ሔጄ ከዕብራውያን ሴቶች ልጥራልሽን አለቻት ። የፈርዖንም ልጅ እሽ አለቻት እህቱም ሔዳ የሕፃኑን እናት ጠራች የፈርዖንም ልጅ ይህንን ሕፃን ወስደሽ አጥብተሽ አሣድጊልኝ ዋጋሽን እሰጥሻለሁ አለቻት ለሚእምኑት ሕጉን ለሚጠብቁት እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ እንደዚህ ያለድንቅ ሥራ ይሠራል ። የሙሴም እናት ልጇን ወስዳ አጠባችው ሕፃኑም አደገ የፈርዖንም ልጅ እኔ ከውኃ አውጥቸዋለሁና ስትል ስሙን ሙሴ ብላ ጠራችው ።

ሙሴ በምቾት ከአደገ በኋላ የፈርዖንን ክብር በፈርዖን ፊት ሹመት ሽልማት አግኝቶ በፈርዖን ቤተ ሰብ ሁኖ





www.ethiopianorthodox.org

መኖርን አልፈለገም እንደወገኖቹ እስራኤል መከራን ችግርን ጭንቀትን ከወገኖቹ ጋር መካፈልን መረጠ እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ነገር ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ሙሴ ከአደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳ ይባል በእምነት እምቢ አለ ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶ አልና የንጉሡን ቁጣ ሣይፈራ የግብፅን አገር የተወ በእምነት ነበር ። ብሎአል ዕብራ. ም. ፲፩ ቁ. ፳፬-፳፯ ።)

ሙሴም ከዚህ በኋላ ወደምድያም በመሰደድ በምድያም የዮቶርን ልጅ አግብቶ የአማቱን የዮቶርን በጎች ሲጠብቅ ሣለ ያ የሚአምነው የእስራኤል አምላክ በኮሬብ ተራራ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድ ቁጥቋጦውም ሣይቃጠል አየ ሙሴም በነገሩ ተገርሞ በመደነቅ ሁኔታውን ለማረጋገጥ ወደዚያ ቦታ ጠጋ ብሎ ለማየት ወደደ እግዚአብሔርም ከቁጥቋጦው ውስጥ ሙሴን ጠርቶ ሙሴ ሙሴ እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው ሙሴም እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው በግብፅ ያለውን ሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ ከአስገባሪዎቻቸው የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ ስቃያቸውንም አይቻለሁ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ እነሆ የእስራኤል ልጆች ጩኸት ወደእኔ መጣ ግብጻውያንም የሚአደርጉባቸውን ግፍ ደግሞ አየሁ አሁንምና ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደፈርዖን እልክሃለሁ አለው ።

ሙሴም እግዚአብሔርን ወደፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ ? ብሎ በመለሰ ጊዜ እግዚአብሔርም እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አለው ከብዙ ጥያቄና መልስ በኋላ ሙሴ በመጨረሻ የጠየቀው ጥያቄ፡ እኔ አፈ ኮልታፋ ምላሴ ጸያፍ የሆንኩ ሰው ነኝ አፈ ትብትብ አይደለምን ብሎ በጠየቀ ጊዜ እግዚአብሔርም ሙሴን የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው? ዲዳስ ፡ ደንቆሮስ ፣ የሚያይስ ዕውርስ የአደረገ ማን ነው ? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን የሚል ማጽናኛ ከነገረው በኋላ ወንድምህ አሮን አፍ ይሆንልሃል በአለው ጊዜ ሙሴ በቀጥታ የፈጣሪውን ትእዛዝ በመቀበል ይህንን ታላቅ ኃላፊነት በመረከብ ወገኖቹ እስራኤልን ከግብፅ ለማውጣት ሄደ ።

ሙሴም ከወንድሙ ከአሮን ጋር በመሆን እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ከፈርዖን ከባድ ቀንበር አገዛዝ ለማውጣት ወደግብፅ ወርዶ ፈርዖንን የዕብራውያን አምላክ እግዚአብሔር ተገለጠልን አሁንም ለአምላካችን ለእግዚአብሔር መስዋዕትን እንሰዋ ዘንድ እንሄዳለንና እግዚአብሔርም ሕዝቤን እስራኤልን ያገለግሉኝ ዘንድ ልቀቅ ይልሃል በአለው ጊዜ ንጉሡ ፈርዖንም እግዚአብሔር ማን ነው ? ሕዝቤን እስራኤልንም አለቅም እግዚአብሔርንም አላውቅም የሚል መልስ ሰጠው ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔርን ኃይል በመያዝ ከ፩-፲ መቅሰፍቶች በማሳየት ወገኖቹ እስራኤልን ከግብፃውያን እጅ ፈልቅቆ ለማውጣት ችሎአል እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ለማውጣት ሙሴ ያን ሁሉ ተአምር ሲአደርግ እያዩ ባለማመናቸው በመጨረሻው በ፲፩ኛው መቅሰፍት (ተአምር) እስራኤል ወገኖቹን በኤርትራ ባሕር መካከል በደረቅ ሲአሳልፍ ግብፃውያን ጠላቶቹን ግን የመጨረሻና የማያዳግም ቅጣት ሰጥቶአቸው አልፎአል ።

ሙሴ እስራኤል ወገኖቹን ከግብፅ ለማውጣት በተላከ ጊዜ ዕድሜው ሰማንያ (፹)ዓመት ነበር እስራኤልም ከግብፅ የወጡት በ፫ሺ፬፻፺፰ ዓ.ም. ላይ ነው ።

ሙሴ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ወገኖቹ እስራኤልን ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደከነአን ለማስገባትና ከነአንን ለማውረስ ፵ ዓመት ሙሉ እየመራ በዚያ ምድረ በዳ በመንከራተት በመጨረሻ ያችን የተስፋ ምድር ሊአወርሳቸው ችሎአል ።

ሙሴ እስራኤልን ፵ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ በቅንነት ሲመራ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ቃል በቃል በመነጋገር ከፈጣሪው ትዕዛዝ ቅንጣት ያህል ፈቀቅ ሳይል ነበር ። እስራኤል ግን ከዚያ መከራና ስቃይ የአወጣቸውን አምላካቸው እግዚአብሔርን በመዘንጋት ሌላ ጣዖት ማምለክም ጀምረው እግዚአብሔርን አስቆጥተው ነበር እግዚአብሔር አምላክም ሙሴን ይህ ሕዝብ በደለኝ ከሥርዓቴ ፈቀቅ አለ ይህንን ሕዝብ ላጥፋና አንተን የሌላ ሕዝብ መሪ አደርግሃለሁ በአለው ጊዜ ሙሴም ቅን ርህሩህ መሪ ስለነበር ይቅር ባይ ፈጣሪውን ይህን ሕዝብ ከምታጠፋ አስቀድመህ እኔን አጥፋ ብሎ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ለመነ ።

እንግዲህ ሙሴ ቅን አስተዋይ ታማኝ ርህሩህ ተወዳጅ መሪ እንደነበር ታላቁ መጽሐፍ ያስረዳናል አሁንም እንደ ሙሴ ያለ ትጉህ ለሕዝብ አሳቢ ተቆርቋሪ እውነተኛ ጠባቂ መሆን ያስፈልጋል ሙሴ ስለእስራኤላውያን ደከመ ለወገኖቹ ደህንነት ከፈጣሪው ለመነ እንጂ እኔን አድነኝ እኔን ከፍ ከፍ አድርገኝ እስራኤላውያን ግን የራሳቸው ጉዳይ አላለም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል አስታራቂ ሆነ እንጂ ሙሴ አምስቱ ብሔረ ኦሪትን ጽፎ የእግዚአብሔር ሕጉንና ትዕዛዙን አስተምሮ አልፎአል በዚህ ሕግና መጻሕፍት እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ ለዓለም በሙሉ መመሪያ ሁኖ ኑሮአል ። ወደፊትም ይኖራል ሙሴ ይህንን ሁሉ ታላቅ ሥራ ከሠራ በኋላ በ120 ዘመኑ ከዚህ ዓለም አልፎአል ።

ስለዚህ ሁላችንም የዚህን ታላቅ ነቢይ እርአያ በመከተል በተጣለብን ኃላፊነት ሠርተን የተቀበልነውን አደራ ተወጥተን በተሰጠን ሕዝብን በቅንነት በታማኝነት በትጋት ተልዕኮአችን መወጣት አለብን ሁላችንም በየተሰማራንበት የሥራ መስክ ከባድ ኃላፊነት እንደተጣለብን አውቀን የያዝነውን ሥራ ሣናቃልል ኃላፊነታችን አውቀን ሥራ ሲወዘፍ ተገልጋዩ ሕዝብ ሲበደል ዝም ብሎ እጁን አጥፎ በምን ችግረኝነት የሚመለከት ሠራተኛ ለሥራ የተሰለፈ መሆኑ ቀርቶ በታሪክም ዘንድ ተወቃሽ ከመሆን አይድንም ሙሴ እስራኤላውያን ወገኖቹ ቢወቅሱት ፡ ሊአጠፉትም ቢሞክሩ አንድ ቀን እንኳን በእስራኤል ላይ በደል አልፈጸመም ፍርድ አላጓደለም ከሥራውም ፈቀቅ አላለም እኛም በዚህ አርአያ በመመራት ኃላፊነታችንን አውቀን የተጣለብንን አደራ ተወጥተን የሚአስመሰግን ሥራ ሠርተን ከመወቀስ ለመዳን ከእያንዳንዳችን ግላዊ ጥረት ይጠበቅብናል ።

ፍሥሐ ባንተ

# የግብርና በረከት

በዛሬው ጽሑፋችን እንደተለመደው በግብርና ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ በሚወጣው ዜና ግብርና ከተባለው መጽሔት ቁጥር ፫ ሚያዝያ ወ ር፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ከታተመው ባለሙያው ይናገር ከሚለው ጽሑፍ ስለማሳና ጎተራ ተባዮች የሾላ አዝርዕት ጥበቃ ላቦራቶርን የሥራ እንቅስቃሴ የሚገልፅ ይሆናል ።

ይህ ላቦራቶር ለግብርናው ልማት ምን ያህል አስተዋጽዖ እንደሚአደርግ ባለሙያው ሲአብራሩ እንዲህ ብለዋል። በላቦራቶሪው በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደው ጥናት የሚአተኩረው በመስክ በሚከናወነው የተባይ መከላከያ ሥራ ላይ ሲሆን ይህም የግብርናው ልማት ግቡን እንዲመታ ይረዳል ተብሎ የሚታመንበት ነው ። በዚህ መሠረት በየክፍላተ ሀገሩ ለማወቅ አሰሳ ይደረጋል ። እንዲህ ዓይነቱ ጥናት በመስክ ደረጃ ጠንካራ የተባይ መከላከል ተግባር ለማካሄድ የሚረዱ ፕሮግራሞችን ለመቀየስ ጠቃሚ ነው ። ይህ ተባይ ከፍተኛ ጥፋት ከመድረሱ በፊት ለመከላከል እንዲቻል ከእርሻ ምርምር ድርጅት ከመንግሥት እርሻዎች ከአ/አ ዩኒቨርስቲና ከአምቦ ዕፀዋት በሽታ ምርምር ላቦራቶር ጋር በመተባበር ተምችን ለመተንበይ የሚያስችሉ መረጃዎች በመብራትና በፌርሞን ወጥመዶች አማካይነት ይሰባሰባሉ እነዚህም መረጃዎች በአሁኑ ጊዜ በኬንያ ወደሚገኘው የምሥራቅ አፍሪካ የተምች ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ማዕከል ተልከው ተምች በየት አካባቢ መቾ ሊነሣ እንደሚችል ጥናት ያደርጋል ሌላው ጥናት የሚካሄድበት ዘዴ በመጠይቆች አማካይነት ነው ። የማሳና የጐተራ ተባዮች በየአካባቢው የሚአደርሱት ጥፋት መጠንና የመከላከያ ዘዴው ምን ያህል አጥጋቢ ውጤት እንደሰጠ ይጠናል ።

ላቦራቶሪው እስከ ዛሬ ድረስ ያከናወናቸው ሥራዎች ሲታዩ ይህ ላቦራቶር እስካሁን የማይናቁ ተግባሮችን እንዳከናወነ ይታወቃል ። ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ቢአስፈልግ በሀገሪቷ ከፍተኛ ጥፋት ያደርሳሉ የሚባሉትን የማሳና የጐተራ ተባዮች ስብስቦ ዓይነታቸው ከተለየ በኋላ በላቦራቶሪው ሙዝየም ለማስተማሪያና ለማገናዘቢያ እንዲያገለግሉ በሥርዓት ተቀምጠዋል ። በአሁኑ ጊዜ በላቦራቶሪው ሙዚየም ፱፻፹ የነፍሳት ተባይ ዝርያዎች ፹ የዕፀዋት በሽታዎች ፪፻፳፭ የአረም ናሙናዎችና ፳፬ የአይጥ ዝርያዎች ተሰብስበዋል ።

የአዝርዕት ጥበቃ ቴክኖሎጅ በልማት ሠራተኞችና ገበሬዎች ዘንድ በሚገባ ለማስራጩት የሚአስችሉ ልዩ ልዩ የተባይ መከላከያ መጽሔቶችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው ሁሉ ተከፋፍለዋል ።

በክፍላተ ሀገር የተመደቡት የአዝርዕት ጥበቃ ባለሙያዎችና የመብራትና የፌርሞን ወጥመድ ኦፕሬተሮች ለገበሬው ጠንካራ የተባይ መከላከያ አገልግሎት ለማበርከት የሚያስችለው የሙያ ማሻሻያ ትምህርቶች ተሰጥተዋል ። ላቦራቶሪው ከጥቃቅን የላቦራቶሪ ዕቃዎችና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ዕጥረት በስተቀር በመሣሪያዎች በኩል በሚገባ የተደራጀ ነው በአሁኑ ጊዜ በላቦራቶሪው ውስጥ ፀረ ሰብል ተባዮችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በትክክል ለመመርመር የሚአስችሉ እንደጋዝ ክሮማቶግራፍ የተባሉ መሣሪያዎች ይገኛሉ ።

ለጥናት ውጤት ተግባራዊነት የገበሬ ማህበራት ተሳትፎ ወሳኝ ነው ገበሬዎች በየአካባቢአቸው ለሚነሱ መደበኛ ተባዮች መከላከያ ናቸው የተባሉት ፀረ ተባዮችና ሌሎች የተባይ መከላከያ ቁሳቁሶች አዘጋጅተው ማከማቸት ይኖርባቸዋል ቀደም ብሎ ዝግጅት ሳይደረግ ቢቀርና ተባይ ቢነሣ አስፈላጊ የተባይ መከላከያ ቁሳቁሶች እስከሚገኙ ድረስ ተባይ ጊዜ ስለማይሰጥ ብዙ ጥፋት ሊደርስ ይችላል ።

ስለዚህ ገበሬው ቀደም ብሎ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀትና ከዚያም ማሳውን ቢአንስ በሣምንት አንድ ጊዜ እየጐበኘ የሰብል ተባዮች መኖራቸውን ና አለመኖራቸውን የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል በዚህም ጊዜ የሰብል ተባዮች ከታዩ ወዲያውኑ ቀደም ብሎ በአዘጋጀው የተባይ መከላከያ ቁሳቁስ በመጠቀም መከላከል ያስፈልጋል እንደዚህ ዓይነት አሠራር ተባዮችን በሚገባ ለመከላከል ከመጥቀሙም በላይ ብዙ የውጭ ምንዛሬ ተከፍሎበት የሚገዛውን ፀረ ተባይ ለመቆጠብ ያስችላል ።

እንግዲህ ላብራቶሪው ወደፊትም ምርታማነትን በበለጠ ለማሳደግና በእርሻ የምርት ውጤት ላይ ጥፋት የሚአደርሱትን የማሳና የጐተራ ተባዮች በቁጥጥር ስር ለማዋል ያላሰለሰ ጥረት ስለሚአደርግ ለዚህ ዓይነቱ አሠራር የእገሌ ድርጅት ይወጣው የሚለውን ዘይቤ ወደኋላ በመተው ሁላችንንም ጉዳዩ



www.ethiopianorthodox.org

"እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው ፡፡ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ከእነርሱም ከእያንዳንዱ ከየአባቶቻቸው ቤት አሥራ ሁለት በትሮች ውሰድ የእያንዳንዱንም ስም በየበትሩ ላይ ጻፍ አንድ በትርም ለአባቶቻቸው ቤት አለቃ ይሆናልና በሌዊ በትርላይ የአሮንን ስም ጻፍ እኔ ከናንተ ጋር በም ገናኝበት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በምስክሩ ፊት አኑራቸው ፡፡ የመረጥሁት ም ሰው በትር ታቆጠቁጣለች አለው ሙሴም እንዳዘዘው አደረገ ፡፡ እንዲህም ሆነ በነጋው ሙሴ ወደ ምስክሩ ድንኳን ውስጥ ገባ እነሆም ለሌዊ ቤት የሆነች የአሮን በትር አቆጠቆጠች ለመለመችም አበባም አወጣች ለውዝም አፈራች "ኦሪት ዘኁልቁ ምራፍ ፲፯ ከቁ ፩ - ፱ ፡፡

የሚያስደንቁ ነገሮችን ተመልክተ ናል ተመርጠው ወደ ምስክሩ ድንኳን የገቡት አሥራ ሁለት በትሮች ሲሆኑ እነዚህም ልምላሜ የተለያቸውና ደረቆች ነበሩ ፡፡ ከነዚህ ሁሉ ተለይታ የአሮን በትር ሳትተከል ውኃ ሳትጠጣ ዝናም ሳይዘንብባት አንዳች እርጥበት ሳታገኝ በእግዚአብሔር ኃይልና ፈቃድ በቅላና ለምልማ አብባና አፍርታ በመገኘትዋ የሰላምና የፍቅር በትር ተብላለች ፡፡

የአሮን በትር የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ሆናለች ቅድስት ድንግል ማርያምም በሷ ተመስላለች ፡፡ ምሳሌነቷም ሁለት መልክ አለው አንደኛው የመጀመሪያው ሰው ወደ ኃጢአት ዓለም በገባበት ወቅት አስቀድሞ የነበረው አካላዊ ቃለ እግዚአብሔር ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለሁ ሲል ተስፋ ሰጥቶት ነበር ፡፡ የተሰጠችውም የተስፋ ልጅ ድንግል ማርያም ነበረች ፡፡

---

ዶመለከተናልና ትብብር ማድረግ ይጠበቅብናል ያለእህል መኖር አይቻልምና ነቢዩም ያለው "አክል ያፀንዕ ኃይለ ሰብእ" እህል የሰውን ጉልበት ያበረታል ነው ፡፡

ፍሥሐ ባንተ

# የሌዊ በትር

ይህችን የተስፋ ልጅ ለማግኘትና ለመውለድ ብዙ ቅዱሳን አበው ተመኝተው ነበር ፡፡ ዕድል ግን አላገኙም ይሁን እንጂ ለብሉይ ጊዜ በሕግና በሥነ ሥርዓት ተጋብተው የኖሩ ኢያቄምና ሐና ልጅ ለማግኘት በጾምና በጸሎት በኀዘን እግዚአብሔርን ተማጸኑ እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ የተስፋ ልጅ የሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ከነሱ እንድትገኝ ቅዱስ ፈቃዱ ሆነ ፡፡ ይህውም በ፭ሺህ ፬፻፹፬ ዓመተ ዓለም ነሐሴ ፯ ቀን ተፀነሰች ፡፡

ምንም እንኳ የመጀሪያው ሰው የልጅ ልጅ ብትሆንም ኃጢአትና መርገም ያልደረሰባት ንጽሐ ጠባይዋ ያላደፈባት እንደ ስንዴ የተለቀመች ንጽሕት ዘር ሁና ቅዱሳን ከሆኑት ከኢያቄምና ከሐና ተፀንሳ የተወለደች ንጽሕት ዘር ናት ከሱዋም የተወለደው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተባረከ ፍሬ ነው ፡፡ ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በደረሰው ውዳሴ ማርያም "የማህፀኑዋ ፍሬ ዓለምን ሁሉ አደነ መርገምንም ከእኛ ዘንድ አጠፋ በመስቀሉና በትንሣኤው በመካከላችን ሰላምን አደረገ" ሲል ተናግሮአል ይህም የቅድስት ድንግል ማርያም መጸነስ የተስፋ ልጅ መሆኑዋን ያበስረናል ይኸውም ደራሲው የአበው ተስፋ በማርያም ድንግል ተፈጸመ" ብሏልና ፡፡

ይህም ብቻ አይደለም ነቢያት ብዙ ትንቢት ተናግረውላታል ብዙ ምሳሌም መስለውላት ነበር ፡፡ ከምሳሌዎቹም መካከል ነቢዩ ሙሴ በሲና ምድረ በዳ በጎቹን አሠማርቶ ሲጠብቅ ሳለ እሳት ሲነድ እየ ቀረብ ብሎ ቢመለከት ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ነበልባሉም ሐመልማሉን ሳያቃጥለው አይቶአል ፡፡ ይህም ማለት አካላዊ ቃል ሥጋን ተዋህዶ በሐመልማላዊት ድንግል ተገልጾ መታየቱን ያስረዳል ፡፡ ሌላው ምሳሌ ደግሞ የኖኅ መርከብ ናት ኖኅ ለመርከቡዋ መገኘት ምክንያት እንደሆነ ሁሉ መርከብዋ ደግሞ ከጥፋት ውኃ ለሚድኑት ሰዎች ታላቅ ምክንያት ሆና ተገኝታለች ከኢያቄምና ከሐና ነሐሴ ፯ ቀን ተፀንሳ የተገኘችውና የተስፋ ልጅ የሆነችው ድንግል ማርያም የመርከብዋ ምሳሌ ስለሆነች ለረጅም ዘመናት በኃጢአት ጠፍተው ለነበሩት ሰዎች ሁሉ የመዳን ምክንያት ሆና ተገኝታለች ፡፡

ኖህም ከመርከብ እንደወጣ መሥዋዕት አቀረበ እግዚአብሔርም የመስዋዕቱ መአዛ ስለጣፈጠ በደስታ ተቀበለው ከእንግዲህ ወዲህ ሰዎችን በጥፋት ውኃ አላጠፋም ሲል ለዘላለም የቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን ቀስቱን በደመና ላይ አደረገ ፡፡ ደመናው የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆን በደመናው ላይ የተደረገው የቃል ኪዳኑ ቀስት ደግሞ ከእርሷ የተወለደው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው ፡፡ ይኸውም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የኃጢአት ግድግዳ አፍርሶ ሰውንና እግዚአብሔርን ያቃራረበውና ያስታረቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በቅዱስ ፈቃዱ ቢሆንም የደመና ምሳሌ የሆነችው ድንግል ማርያምም ለመውለድ ምክንያት ሆና ተገኝታለች ፡፡


ነሐሴ ፯ ቀን ከኢያቄምና ከሐና ተፀንሳ የተገኘችውን ምሳሌዋም ደመና የሆነችው (የአሮን በትር የሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ለምእመናን የቃል ኪዳን ምልክት እና እናት ሆና ተሰጥታለች ይኸውም በሱና በእኛ መካከል ስላለው መንፈሳዊ ችግር በልዩ ልዩ ኃጢአት በጸሎት በኀዘን በአማላጅነት እየ ቀረበች የምታማልደንና ለችግራችን መፍትሔ የምታስገኝልን መንፈሳዊት እናታችን ስለሆነች ልንወዳትና ልናከብራት ይገባናል ፡፡

እስካሁን የዘረዘርነው አንደኛውን ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአሮን በትር ሳትተከል ውኃ ሳትጠጣ ፥ በቅላ አቆጥቁጣና አለምልማ አብባና አፍርታ እንደተገኘች ሁሉ የክህነትና የሰላም የሆነችው የዚችው በትር ምሳሌና ከኢያቄምና ከሐና ተጸንሳ የተገኘችው ድንግል ማርያምን በመቅደመ ተአምርዋ "እምቅድመ ዓለም ነበረት በሕሊና አምላክ" ሲል ያወድሳታል ትርጉሙ እመቤታችን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በህሊና አምላክ ነበረች ማለት ሲሆን በልበ አምላክ ታስባና ተዘጋጅታ የተቀመጠች መሆኑዋን ያመለክታል ዓለም ከተፈጠረ ወዲህ ደግሞ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንኃለሁ ባለው መሠረት ለዓለም ሁሉ የተስፋ ልጅ ሆና ኖራለች ፡፡

እንደተወለደችም የሥዕለት ልጅ ስለነበረች ለእግዚአብሔር ተሰጠች እንደሱዋ ለሥዕለት የተሰጡ ብዙ የእስራኤል ደናግል ነበሩ ፡፡ ድንግል ማርያም ግን በንጽሕና በቅድስና በርኅራኄና በትሕትና ከሁሉ የላቀች ከመሆኑዋም ሌላ ሰውን የምትወድና ሰውም የሚወዳት በአማላጅነትዋም ከሁሉ በላይ በመሆንዋ ፡፡ ለክርስቶስ እናትነት ተመረጠች መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም "ደስ ይበልሽ ፀጋ የሞላብሽ ሆይ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይፀልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሲል አበሰራት (ሉቃስ. ምዕ. ፩ ከቁ ፳፰ - ፴፭)

በዚህ አኳኋን እንደ አሮን በትር ያለ ምንም ምክንያት መልአኩ እንዳበሰራት አምላክን በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ በመንፈስ ቅዱስ ስለወለደች ከሴቶች ሁሉ የተረከበች ሆና ተገኘች ፡፡

አለቃ ነቢዩ ልዑል ዮሐንስ







www.ethiopianorthodox.org

# ለዶርዜ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ኤሌክትሪክና የድምፅ ማጉሊያ መግባቱ ተገለጠ

በጋሞ ከፋ ክፍለ ሀገር በጋሞ አውራጃ በጨንቻ ወረዳ የሚገኘው የዶርዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፭ሺ.ህ ብር በተሠራው ጀኔሬተር (ሞተር) አማካይነት

፩ኛ/ ፴ አምፑል ያለው የኤሌክትሪክ መብራት፡

፪ኛ/ በቤተ ክርስቲያኑ በ፫ ማዕዘን የተሠራ የድምፅ ማጉሊያ ገብቶለት አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆኑን መምሬ ሽታ ከበደ የጋሞ አውራጃ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ በላኩት ሪፖርት ገልጠዋል ።

ጀኔሬተሩን በገንዘባቸው ገዝተው በራሳቸው ወጭ በማጓጓዝ እዚያም ከደረሰ በኋላ በሚገባ ተገጣጥሞ የኤሌክትሪክ መብራት እንዲሰጥ በማድረግና የድምፅ ማጉሊያውን ገዝተው በሦስቱ ማዕዘን በማስገጠም ከግል ገንዘባቸው ብር ፲፭ሺ. (አሥራ አምስት ሺህ ብር) በማውጣት ይህንን የመሰለ በጎ አድራጎትና ክርስቲያናዊ ተግባር የፈጸሙት ነዋሪነታቸው አዲስ አበባ የሆነው የዚሁ የዶርዜ ሀርጵ ቀበሌ ተወላጅ የሆኑት አቶ መኩሪያ መልሳሞ የተባሉት ግለሰብ መሆናቸውን ሪፖርቱ ጠቅሶ ተጠቃሹ በጎ አድራጊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸውን ከመልካም ምግባር ጋር አስተባብረው የያዙ መሆናቸውን ይኸው መልካም አድራጎታቸው በግልጥ የሚያስረዳ መሆኑን አመልክቷል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በ፪ኛው መልእክት ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፫ ላይ የሚቻላቸውን



አቶ መኩሪያ መልሳሞ

ብቻ ሳይሆን ከሚቻላቸውም በላይ በፈቃደኝነት እንዲሰጡ እኔ እመሰክርላቸዋለሁ በማለት እንደገለጸው ሁሉ አቶ መኩሪያ መልስሞም የትውልድ ሀገራቸው ለሆነው ለዶርዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ በ፲፭ሺ.ህ ብር ወጭ ያበረከቱት መንፈሳዊ አገልግሎት ቀላል ባለመሆኑ ይህንኑ የቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ መልእክት ተግባባራዊ ለማድረግ በዓቅማቸው መጠን ብቻ ሳይሆን ከዓቅማቸው በላይ በፈቃደኝነት የሰጡ ለመሆናቸው ስጦታው ራሱ ምስክር ነው ፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር የሚወደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለሆነ እያንዳንዱ የሚሰጠውን በልቡ ፈቅዶ በደስታ ይስጥ እንጂ እየተፀፀተ አይስጥ'' ሲል ሐዋርያው በዚሁ መልእክቱ ምዕራፍ ፱ ቁጥር ፯ ላይ እንዳረጋገጠው ሁሉ አቶ መኩሪያ መልሳሞም ማንም ሳያስገድዳቸው በራሳቸው ፈቃድ ብር ፲፭ሺ. ከግል ገንዘባቸው አውጥተው ይህን ታላቅ ሥራ መሥራታቸው የእግዚአብሔርን ቤት ከራሳቸው አብልጠው የሚወዱ በመሆናቸው ስለሆነ የሚመሰገኑና ለሌሎችም መልካም አርአያ የሚሆኑ እውነተኛ ክርስቲያን መሆናቸውን መምሬ የሽታ ከበደ በላኩት በዚሁ ሪፖርታቸው ጠቁመዋል ።

አቶ መኩሪያ መልሳሞ በዚሁ አውራጃ ከአርባ ምንጭ ወረዳ በመሠራት ላይ ላለው የደጋ አቆሎ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ብር ፩፻፶ (አንድ መቶ ሃምሳ ብር) የሰጡ መሆናቸውን በእጃቸው የሚገኘውን የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ አይተን ከመረዳታችንም በላይ ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም የሚቻላቸውን ያህል እርዳታ እያደረጉ መሆናቸውን ላአቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ለመገንዘብ በቅተናል ።

ስለዚህ ግለሰቡ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን የተወጡ በመሆናቸው ይህንኑ መልካም ተግባራቸውን ቤተ ክርስቲያን አትዘነጋውምና ዘወትር በጸሎት ታስባቸዋለች ።

የዶርዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ ያሉት የሀገር ተወላጆች ባደረጉት አስተዋጽኦና በሀገሬው ምእመናን ትብብር አስደሳች የሆነ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ አገልግሎት እየተፈጸመበት መሆኑ የሚታወስ ነው ። ስለሆነም በአካባቢው የኤሌክትሪክ መብራት ባለመኖሩ በቅርብ ቀን መብራትም ሆነ የድምፅ ማጉሊያ ይገባለታል የሚል ግምት አልነበረንም ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን በጎ አድራጊዎችን ማስነሣት ልማዱ ነውና መንፈስ ቅዱስ አቶ መኩሪያ መልሶሞን አነሣስቶ ለመልካምና ለመንፈሳዊ ተግባር ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ለቤተ ክርስቲዳኑ የኤሌክትሪክ መብራትና የድምፅ ማጉሊያ በመግባቱ የዶርዜ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ካህናትንና ምእመናንን እንኳን ደስ አላችሁ እንላቸዋለን ከዚህም ጋር የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች ቀሳውስትና ዲያቆናት በአጠቃላይ ምእመናኑ ሁሉ ለዚሁ መሣሪያ ጥንቃቄ ያደርጉ ዘንድ አደራ እንላቸዋለን።

## ዜና ዕረፍት

ወ/ሪት ሣራ ገብሬ ከአባቷ ከአቶ ገብሬ አልዋቤ ከእናቷ ከወ/ሮ አመለዘውድ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ግንቦት ፲፱ ቀን በወሎ ክ/ሀገር በደሴ ከተማ ተወለደች ።



ወ/ት ሣራ ገብሬ

ሣራ እድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰ በቄስ ት/ቤት ፊደልን ለይታ ካወቀች በኋላ በቀጥታ ወደ ዘመናዊ ት/ቤት በጊዜው እቴጌ መነን ት/ቤት ይባል በነበረው ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ከተማረች በኋላ ከዚያም ወደ ቅዳሜ ገበያ ት/ቤት ገብታ የ7ኛንና የ8ኛን ክፍል ትምህርት አጠናቃለች ። እንዲሁም በሆጤ ት ቤት የ9ኛ ክፍል ትምህርቷን ፈጽማለች ።

በእነዚህ የትምህርት ዘመኖቿ ታሳያቸው የነበሩትን ውጤቶች ዘወር ብለን ወደ ኋላ ስንመለከት ይህች ታዳጊ ወጣት ይህን ያህል ውጤት ይኖራታል ብሎ ለማመን ያስቸግራል ። ይሁን እንጂ ያኗትን የምሥክር ወረቀቶቿን ስንመረምር በክፍሏ ከሚገኙት ተማሪዎች መካከል ከ፩ኛ እስከ ፫ኛ ባሉ ደረጃዎች መካከል ብቻ በመውጣት ያለፈች መሆኑን ያረጋግጣል ። ሣራ በት/ቤት ውስጥ ከመምህራኖችም ሆነ ከክፍል ጓደኞቿ በየጊዜው ምስጋናና አድናቆትን ከማግኘቷ በስተቀር አንድም ቀን ከሥነ ሥርዓት ውጭ በመሆን ማንንም አስቀይማ እንደማታውቅ የቅርብ ተመልካቾቿ ሁሉ ያረጋግጣሉ ። ሣራ በ፲፱፻፸፮ ዓ.ም ደሴ በሚገኘው የካቲት ፷፮ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ፲ኛ ክፍል ትምህርቷን በመከታተል ላይ ትገኝ ነበር ።

በተለይም ይህች ወጣት በታላቁ ደብር በደሴ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኘው የወልድ ዋህድ ወጣቶች የሰንበት ት/ቤት አባል በመሆን ከ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ የሰንበት ት/ቤት እንዳሳለፈች ታሪኳ ያረጋግጣል ። ስለ ሣራ የቅርብ ጓደኞቿ ሲናገሩ ''ሣራ እህታችን ብቻ ሳትሆን አስተማሪያችንም ነበረች'' ፡ ሣራ እህታችንም ብቻ ሳትሆን እናታችንም ነበረች ሲሉ ሌሎች ደግሞ ''ሣራ ተስፋችን ናት ፡ ሣራ ደስታችን ናት ፡ ሣራ ምሳሌአችን ፡ አይናችን ነበረች'' እያሉ ይናገሩላት ነበር።በተለይም በተሰጣት አምላካዊ አእምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሃይማኖቷን ምንነት መረዳት የቻለች ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ፈጽማ ያወቀች በዚህ በልጅነት ዕድሜዋ አጽዋማትን አጠናቃ የምትጾም በጸሎት የተጋች እውነተኛዋ የተዋህዶ ልጅ እንደነበረች የታወቀ ነው በማህበር ውስጥም ከትልቁ ጋር ትልቅ ፡ ከትንንሾቹ ጋር ትንሽ በመሆን ከሁሉ ጋር ሰላምና ፍቅር ተወዳጅነት የነበራት እህት ስትሆን ማኅበሩ በሚያዘጋጀው ዝግጅትም ሁሉ በተፈለገችበት ቦታ ያከመኝ ፈቃደኛ አያደለሁም ፡ አልችልም የሚሉ ቃላቶች ከአፏ ሳይወጡ በትጋት የምትሰራ ከመሆኗም በላይ በማኅበሩ ውስጥ የሕጻን ክፍል የቅዱስ ዮሐንስ ቡድን ሊቀ መንበር በመሆንና በኋላም ቡድኑ በዕውቀትና በዕድሜ ሲያድግ የቅዱስ ሉቃስ ቡድን ሊቀ መንበር በመሆን መሰል እህቶቿንና ጓደኞቿን በማስተባበር ትሠራ ነበር ።

ሣራ በተለይ መንፈሳዊ ውድድሮች ሲደረጉ ሁልጊዜ የአንደኝነትን ደረጃ የምትይዝ ስትሆን ከሁሉ በጣም የሚያስደንቀው ሣራ በበዓላተ ንግሥ ላይና በጥምቀት ፡ በቃና ዘገሊላ በመሳሰሉት ዓበይት በዓላት ላይ ተገኝታ ወጣቶች ለዘብ በሚያለዝቡበት ሰዓት መቋሚያዋን ከጸናጽሉ ጋር ይዛ በተመስጦ ስትዘምር እውነተኛዋ የቅዱስ ያሬድ ደቀ መዝሙር እንደምትመስል ብዙዎች ይናገሩላት ነበር ።

በውነትም ስምን መልአክ ያወጣዋል እንደተባለው ሣራ የስም ሣራ ብቻ ሳትሆን በዚህ አጭር ዕድሜዋ የትልቋ ሣራ የምግባር ልጅ ነበረች ። ለዚህም ነው ዛሬ የማህበሯ ልጆችና ሌሎችም የሚያውቋት ሣራዬ ፣ ሣራዬ በማለት በዕንባ ሲራጩ የሚታየው ። ታዲያ ምን ይደረግ እግዚአብሔርም እንደሰው ወደዳትና በዚህ ዓለም እግዚአብሔር አምላኳን በጾም በንጽህና በድንግልና እንዳመሰገነችው በወዲያ ዓለምም ከቅዱሳት ደናግል ጋር በቅድስና በድንግልና እንድታመሰግነው ስለወደደ ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ጀምሮ በደረሰባት ድንገተኛ ህመም በተለያዩ የህክምና ቦታዎች ስትረዳ ቆይታ በፍጹም ሊሻላት ባለመቻሉ የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም አርፋ የካቲት ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው በደብረ ገሊላ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ዘመድ

ተከታዩ ወደ ገጽ ፲፪ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ዳግም ምጽአት

ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በዓመት ፫ ጊዜያት ከምታስታውሳቸው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፩ኛው በኅዳር ወር አስተምህሮ የተባለው ነው ፪ኛው በዓቢይ ጾም አጋማሽ የሚገኘውና ደብረ ዘይት በመባል የታወቀው ሲሆን ፫ኛው ደግሞ በዓመት መጨረሻ የምትገኘው ወርኃ ጳጉሜን ናት ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው ሰው በፈጸመው በደልና በሠራው ኃጢአት ምክንያት ያነን የፈጸመውን በደል ለመደምሰስ ከሰማያዊ ዓለም ወደ ምድራዊ ዓለም መጥቶ ፍጹም አምላክ ሲሆን ፍጹም ሰው ሁኖ የተሠራውን ኃጢአት ሠርዞ የሞትን ኃይል ደምሰሶና ድል ነሥቶ በተነሣ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ በሚያርግበት ወቅት ደቀ መዛሙርቱ ዓይናቸውን ወደሰማይ አቅንተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲመለከቱ አይተው ሁለት (መላእክት ) የክብር ባለቤት ክርስቶስ ዳግመኛ እንደሚመጣ ሲያመለክቷቸው እናንተ የገሊላ ሰዎች ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እንዴት ትቆማላችሁ ይህ ከእናንተ ተለይቶ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት ሁሉ እንዲሁም ዳግመኛ ይመጣል ብሏቸዋል የሐዋ.ሥራ ፩፡፲፩ አዎ የዓለም መድኀን ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል ስንል የፊተኛው አመጣጡና የዳግም አመጣጡ የተለያዩ ናቸው ።

ይኸውም ከዚህ በፊት የመጣው ሰው ሆኖ ራሱን ዝቅ አድርጎ ትሕትናን ለብሶ ነበር ። ዳግመኛ ሲመጣ ግን በታላቅ ግርማና በአስደንጋጭ አመጣጥ ነው የማመጣው የያዕቆብ ወንድም የሆነው ይሁዳም ስለ ዳግም ምጽአት አስመልክቶ ከሄኖክ ጠቅሶ ሲናገር "እነሆ ጌታ በኃጢአተኞች እንዲፈርድና ኃጢአተኞችን እንዲወቀስ ከአእላፍ ቅዱሳን ጋር ይመጣል ሲል መስክሮአል ይሁዳ ፩-፲፬


የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ወደ ዓለም ሲመጣ እንዲሁ አይደለም በሃይማኖታቸው ጸንተው ፈቃዱንም ፈጽመው በመንፈሳዊ መንገድ ሲራመዱ ለነበሩት ቅዱሳን የድካማቸውን ዋጋ ለመስጠት ሲሆን በዚሁ አንጻር ደግሞ ከሕጉ ወጥተው ሃይማኖታቸውን ረስተው እግዚአብሔርን ሲያሳዝኑ የተፈጥሮ ጓደኞቻቸውን ሲያስቀይሙ ለነበሩት ኃጢአተኞች ደግሞ ፍዳቸውን ለመስጠት ነው የሚመጣው ።

ዳግም ምጽአት መንፈሳዊ ሥራ ሠርቶ የተገኘ የሚደሰትበት ሲሆን መንፈሳዊና መልካም ሥራ ሳይሠራ የተገኘ ደግሞ የሚያዝንበትና የሚያለቅስበት ጊዜ ነው ።

ምክንያቱም (ወድል ዋኒከሙ ህልው) እንሆ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ጌታ በየትኛው ሰዓተ መዓልት ወይም በየትኛው ሰዓተ ሌሊት እንደ ሚመጣ አታውቁምና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ባለው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ተዘጋጅተው የኖሩ ሁሉ ከክብር ወደ ክብር ስለሚሄዱ ምጽአቱን መቼ ነው የሚደርሰው በማለት ሲናፍቁት ይኖራሉ ። በሥራ ያልተገኙ ግን ከሥቃይ ወደ ከፍተኛ ሥቃይ ስለሚሄዱ ያዝናሉ ያለቅሳሉ ነቢዩ ዳንኤልም ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ሲል ገልጾአል ። "በምድርም ትቢያው ስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ይሄዳሉ ብሏል ዳን.፲፪፡፪-፫ ።

የሠራ ይደሰትበታል ፣ ያልሠራ ያዝንበታል ያልነውም ከዚህ የተነሣ ነው። ሥጋዊ ሥራም ሆነ መንፈሳዊ ሥራ የሰውን ችግር የሚያስወግድ መሆኑን ሁላችን ልንገነዘብ ይገባል ።

በሥጋዊ ሥራ ያልተሠማራ ሰው ሁሉ የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን እንደ ማያገኝና የሰውን እጅ ከመመልከት ነፃ እንደማይሆን ሥውር አይደለም። ነገር ግን ባጭር ታጥቆ በሮቹን ጠምዶ እርፉን ጨብጦ ወደ ሥራ የሚሠማራ ከቤቱ እህል አያጣም ከዚህ አልፎ ተርፎ ራሱንና ቤተሰቦቹን ችሎ ሌሎችን የሚረዳ መሆኑ የታወቀ ነው ።

በዚህ አንጻር ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ባለው መሠረት ጌታዬ መቼ ይመጣ ይሆን በማለት ተዘጋጅቶ የሚኖረው ሰው የተመኘውን አያጣም ተስፋ ያደረገውንም ነገር ሁሉ ለማግኘት ይችላል ዘለዓለማዊ ሕይወትን ሰማያዊ ክብርን የሚያገኘው በነዘህላልነት የነበረና ወርቃዊ ጊዜውን በከንቱ ያሳለፈ ሳይሆን ጊዜውን ሁሉ በሥራ ያሳለፈ ሁኖ የተገኘ ነው ። የሰው ልጅ ምን ይመጣብኛል ብሎ ተዘልሎ ከመኖር የሚመጣው ነገር አይታወቅምና መዘጋጀት አለብኝ ብሎ ተዘጋጅቶ ሲኖር ነው ግርማንና ሞገስን የሚለብሰው አንዳንድ ሰዎች ምጽአት ማለት ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ነው ሌላ ምጽአት የለም ብለው ያስባሉ ግን የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ነው ሰው ከሞተና ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ መነሣት እንዳለበት መጻሕፍት ይመሰክራሉ ።

እንዲያውም ስለ ምጽአትና ስለ ትንሣኤ ሙታን አውስቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር የቆሮንቶስ ሰዎች እንደ ጠየቁትና እሱም እንዲህ ሲል እንደ መለሰላቸው እናስታውሳለን ።

"ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ ? የሚል ይኖር ይሆናል ካለ በኋላ መልሱን በምሳሌ ሲያስረዳ አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው እንኳ ካልሞተ (ካልፈረሰና ካልበሰበሰ) ሕያው አይሆንም አይነሣም ሲል አስረድቷል ።

አሁንም ዘርና ሰው በመልክ ይለያይ እንጂ የአነሣሱም ሁኔታ አንድ ነው ታዲያ በምጽአት ጊዜ በየመቃብሩ የተዘራ የሰው ሁሉ አካል ተነሥቶ በጌታ ፊት ይቆማል ከላይ እንደ ገለጽነው በሚነሱበትም ወቅት ሥራ ሥራውን ይዞ ነው የሚነሣው ።

በጎ የሠራ ብርሃንን ለብሶ ብርሃን ተጎናጽፎ ሲሆን ክፉ ሥራንም የሠራ ጨለማን ለብሶ ጨለማንም ተጎናጽፎ ይነሣል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣውም ለደጋጎቹ ዋጋቸውን ለክፉዎቹ ፍዳቸውን ለመክፈል ስለሆነ ብርሃንን ለብሰው ለተነሱት የማያልፈውን ሰማያዊ ልብስ አልብሶ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሲመራቸው ጨለማን ለብሰው ለተነሱት ደግሞ ሐፍረትንና ኃዘን በማልበስ ወደ ዘለዓለማዊ ጉስቁልና አሳልፎ ይሰጣቸዋል ።

ቃሉ የሰው ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚያስረዳን ይኸውም እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ሲላቸው እንደዚሁ ደግሞ በደለኞችን እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ ሲል ያሰናብታቸዋል ማቴ ፳፭.፴፬-፵፪ ።

እንግዲህ ምጽአት ሲባል መልካም የሠራ ዋጋውን የሚያገኝበት ሐኬተኛም ቅጣቱን የሚቀበልበት ጊዜ ነውና እያንዳንዱ ተዘጋጅቶ መጣባበቅ ይኖርበታል ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ

# የዘመን አቆጣጠር

ከገጽ ፳፬ የዞረ

ዟል ግንቦት አሥራ አምስት በዓለ ዕርገት ይሆናል የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ ነው ሃያ ስምንትና ሃያ ሰባት ሃምሳ አምስት ይሆናል ሰላሣውን ገድፎ ሃያ አምስት ይቀራል ግንቦት ሃያ አምስት ቀን በዓለ ጰራቅሊጦስ ይሆናል ።

የጾመ ሐዋርያት ተውሳክ ፳፱ ነው ፡ ሃያ ዘጠኝና ሃያ ሰባት ሃምሳ ስድስት ፡ ሰላሣውን ገድፎ ግንቦት ሃያ ስድስት ጾመ ሐዋርያት ይሆናል የጾመ ድኅነት ተውሳክ አንድ አንድና ሃያ ሰባት ፡ ሃያ ስምንት ግንቦት ሃያ ስምንት ጾመ ድኅነት ይሆናል ። እግዚየአብሔር ሐዲሱን ዘመን የበረከትና የሰላም ዘመን ያድርግልን አሜን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ





www.ethiopianorthodox.org

# የዘመን አቆጣጠር መቼ ተጀመረ?

ይህ ርዕስ ሆኖ የቀረበው ቃል ጥያቄን ያስከተለ መሆኑ ግልጽ ነው ለዚህም ምልሱ ቅርብ ሳይሆን አይቀርም የዘመን አቆጣጠር ከሥነ ፍጥረት ጋራ አብሮ በተከታታይ እየተጓዘ እስከ አለንበት ዘመን ደርሷል ።

በመሠረቱ ዓለም የተፈጠረ በዕለተ እሑድ መሆኑ ታውቋል ። እሑድ ማለትም አንድ ማለት ነው በግዕዝ እሐደ አንድ አደረገ ካለው የወጣ መሆኑ ግልጽ ነው እንግዲህ አንድ ካልተባለ ሁለት የለምና ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዓርብ ያሉ ዕለታት ስድሥት ናቸውዓርብንም ስድስተኛ መሆኑን ሲያስረዳ ስዱስ መዋዕለ ግበሩ ግብረክሙ ይላል ።

ዕለተ ቀዳሚትም ሰባተኛ እንደሆነች ሲገልጽ አመ ሳብእት ዕለት እረፍተ ትኩንክሙ ይላል እንግዲህ ከእሑድ እስከ ቀዳሚት ሰባት ቀን ይሆናል ሰባት በዕብራውያን አቆጣጠር ፍጹም ነው። ሰባቱ ዕለታትም አንድ ሱባኤ ተብለው ይቆጠራሉ ሰባቱንም ሱባኤ አንድ ኢዮቤልዩ እያሉ ይቆጥሩት እንደነበር በሱባኤ አዳም ይታወቃል ።

በሌላ በኩልም ሰባቱን ሱባኤ ዓመታት አንድ ኢዮቤልዩ እያለ ነቢዩ ሙሴ ይቆጥርበት እንደነበር ታውቋል ከነቢያትም ዕዝራና ኤርምያስ እግዚአብሔር ወልድ ወደ ዓለም እንደሚመጣ ስለተገለጸላቸው አምስቱን ሺህ አምስት መቶ ዘመን ቆጥረው እንደተረዱት ይተረካል በሌላ በኩልም የዘመን መለወጫ በመስከረም ወር የተጀመረ ከድሜጥሮስ ወዲህ ነው የሚሉ አሉ ወደ ብሉይ ኪዳን መለስ ብለን ብንመለከት ግን በኖኅ ዘመን በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውሃው ከምድር እንደደረቀና ኖኅም የመርከቡን ክዳን እንዳነሣ በሁለተኛው ወር በሐያ ሰባተኛው ቀን ምድር እንደታየች ይነገራል ። ዘፍጥረት ፰ ቁ. ፲፬ ።

ይህንን ንባብ ስንመለከተው አንደኛው ወር የተባለ መስከረም እንደሆነ እንረዳለን ፣ ሁለተኛ ወር የተባለው ጥቅምት ሲሆን በሁለተኛው ወር በሃያ ሰባት ቀን የተባለም ጥቅምት ሃያ ሰባት ቀን መሆኑ ተብራርቷል ። ይህም መስከረም የዘመን መለወጫ መሆኑ ከኖህ ዘመን እያይዞ እንደመጣ ያስረዳል ።

በሐዲስ ኪዳን ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በዚያን ጊዜ የነበሩ ካህናትና ምዕመናን በእየ ዓመቱ በዓለ ትንሣኤን መጋቢት 29 ቀን እያከበሩ እስከ መቶ ሰማንያ ዓመት ቆይተው ነበር ከመቶ ሰማንያ ዓመት በኋላ ግን በቅዱስ ማርቆስ ወንበር አሥራ ሁለተኛ ሆኖ የተሾመው ድሜጥሮስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተገልጾለት ባሕረ ሃሣብን እንደደረሰና አጽዋማትና በዓላት ከጥንት ይውሉበት ከነበረው ዕለት ለየት ባለመንገድ ማለትም ትንሣኤ ከእሑድ ስቅለት ከዓርብ ወዘተ ሁሉም በዚያው እንዲውሉ ወስኗል ።

ባሕረ ሃሣብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው ቤተ ክርስቲያናችንምየድሜጥሮስን አቆጣጠር ተግባራዊ አድርጋ ስታስተምር ኑራለች ዛሬም ይህንኑ ይዛ ትገኛለች የቤተ ክርስቲያናችን አቆጣጠር እንግዳ ባይሆንም እንደተለመደው ለመግለጥ ቢያስፈልግ ሰባቱን ሺህ አምስት መቶ ሰባ ሰባት ዘመን በዓበይ ቀመር በማዕከላዊ በንዑስ ይከፈላል ዓበይ ቀመር መደቡ አሥራ ሶስት ለእያንዳንዳቸው የሚሠጣቸው ቁጥር አምስት መቶ ሰላሳ ሁለት ማዕከላዊ ቀመር መደቡ ስድስት የሚሠጣቸው ቁጥር ሰባ ሰባ ስድስት የንዑስ ቀመር መደቡ አምስት የሚሠጠው ቁጥር አሥራ ዘጠኝ ከዚህ የተረፈው ተረፈ ዘመን ይባላል ።

እንግዲህ በሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት ዓመተ ምሕረት በዘመነ ማቴዎስ መስከረም ማክሰኞ ይብታል በተውሣክ የሚወጡ አጽዋማትና በዓላት የሚውሉበትን ለማወቅ ተረፈ ዘመን አስር ይሆናል አሐዱ አእትት ለዘመን ስለ ተጀመረ ተቀጠረ ስለአስተፈጸመ ታተተ ብለን እንዱን ትተን ዘጠኝ ወንበር እንይዛለን ።

ሃያ አንድ መጥቅዕ ዘጠኝ አበቅቴ ይሆናል መጥቅዕ መስከረም ፳፩ ቀን ይውላል ዕለቱ ሰኞ ይሆናል የሰኞ ተውሳክ ስድስት ስድስትና ፳፩ ሃያ ሰባት መባጃሐመር ይሆናል ጥር ሃያ ሰባት ጾመ ነነዌ ፤ የዓቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ አሥራ አራትና ሃያ ሰባት ፵፩ ይሆናል ሰላሣውን ገድፎ የካቲት አሥራ አንድ ዓቢይ ጾም ይገባል ። የደብረ ዘይት ተውሳክ አሥራ አንድ ፤ አሥራ አንድና ሃያ ሰባት ሠላሣ ስምንት ፤ ሰላሣውን ገድፎ ስምንት ይቀራል መጋቢት ስምንት ደብረ ዘይት የሆሣዕና ተውሳክ ሁለት ነው ።ሁለትና ሃያ ሰባት ሃያ ዘጠኝ ይሆናል ። መጋቢት ሃያ ዘጠኝ ቀን ሆሣዕና ይውላል፤ የስቅለት ተውሳክ ሰባት ሰባትና ሃያ ሰባት ሰላሣ አራት ሠላሣውን ገድፎ ሚያዚያ አራት ቀን ስቅለት የትንሣኤ ተውሣክ ዘጠኝ ነው ዘጠኝና ሃያ ሰባት ሰላሣ ስድስት ይሆናል ። ሰላሣውን ገድፎ ሚያዚያ ስድስት ቀን በዓለ ትንሣኤ ይሆናል ።

የርክበ ካህናት ተውሳክ ሃስት ሶትና ሃያ ሰባት ሠላሣ ፤ ሚያዚያ ሰልሣ ርክበ ካህናት ይሆናል የዕርገት ተውሣክ ፲፰ ነው አሥራ ስምንትና ሃያ ሰባት ፵፭ ይሆናል ሠላሣውን ገድፎ ፲፭ቱን ይይ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org